የኢትዮጵያ

ሕገ መንግሥት

-ረቂቅ-

ከከፍተኛው ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ ጉባዔ ፡ የቀረበ

ሐምሌ ፡ ፴ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፸፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡

የ ኢ ት ዮ ጵ ያ

ሕ ገ መ ን ግ ሥ ት

/ረቂቅ/

ከ[illegible] ሕገ መንግሥታዊ ጉባኤ የቀረበ

ሐምሌ 30 ቀን 1966 ዓ.ም.

ምዕራፍ አንድ

ስለ ብሔረ ኢትዮጵያና ስለ ዜጎች

ክፍል — 1

ስለ ብሔረ ኢትዮጵያ

አንቀጽ 1:

1. ብሔረ ኢትዮጵያ በኢትዮጵያ ሕዝብ ሙሉ ነፃነት ሥር የሚገኘውን አገር ሁሉ፣ ባሕርን፣ ደሴትን፣ ጠረፍን ጭምር ያጠቃልላል።
2. በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ በውጭ አገር የሚኖር ኢትዮጵያዊ ሁሉ በአንድነት የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው። ለመንግሥቱ ሥልጣን ምንጩ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው።
3. አገሪቱም ሆነች የሕዝቡ ሙሉ ነፃነት አይነጣጠሉም፤ ለሰላም አይለዩ

አንቀጽ 2:

የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ከላይ አረንጓዴ፣ ከመሀከል ቢጫ፣ ከታች ቀይ ነው። ሦስቱም ቀለማት እኩል ሆነው በአግድም ይቀመጣሉ። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

አንቀጽ 3:

የኢትዮጵያ ዋና ከተማ አዲስ አበባ ነው።

አንቀጽ 4:

ስለ ኢትዮጵያ ቋንቋዎች በሌሎች አንቀጾች የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የኢትዮጵያ መንግሥት መደበኛ ቋንቋ አማርኛ ነው።

./.

አንቀጽ 5፡

1. ኢትዮጵያ በሕግ በተወሰነ የዘውድ መንግሥት የምትተዳደር፣ ሠርቶ በመኖርና በሕዝብ የሀብትና የኑሮ ተመጣጣኝነት ዓላማ የመሠረተች ናት፡፡

2. የኢትዮጵያ መንግሥት የሕግ አውጪ፣ የአስፈጻሚና የዳኝነት ዘርፎች ይኖሩታል፡፡

አንቀጽ 6፡

1. የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ባለሥልጣኖች በዚህ ሕገ መንግሥት መሠረት ከሚሰጣቸው ሥልጣን በቀር ሌላ ሥልጣን አይኖራቸውም፡፡ ሕጉን ተከትለው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቅም ብቻ መሥራት ግዴታቸው ነው፡፡

2. ማንኛውም ባለሥልጣን በሕገ ወጥነት ወይም ሥልጣኑን መከታ በማድረግ ስለፈጸመው ወንጀሉ ተገቢ ተጠያቂ ነው፡፡

ክፍል — 2

ስለ ዘውዱ

ንኡስ ክፍል — 1

ስለ ንጉሠ ነገሥቱ

አንቀጽ 7፡

ንጉሠ ነገሥት የኢትዮጵያ ርእሰ ብሔርና የሕዝቧ አንድነትና የታሪኳ ምልክት ነው፡፡ ሥልጣኑና ተግባሩም በዚህ ሕገ መንግሥት እንደተወሰነው ይሆናል፡፡

./.

አንቀጽ 8፡

ንጉሠ ነገሥቱ የአገሪቱ ርእሰ ብሔር በመሆኑ ክብሩ የማይቀነስ፣ ግዑ ርጉም የማይገሠሥ ነው። ማንኛውም ሰው ቢሆን በንጉሠ ነገሥቱ ላይ ክስ ማቅረብ አይችልም። ንጉሠ ነገሥቱ ለሚፈጽማቸው ብሔራዊ ጉዳዮች ተጠያቂ የሚሆኑት በኃላፊነት የሚሾሟቸው ባለሥልጣኖች ናቸው።

አንቀጽ 9፡

1. የንጉሠ ነገሥቱ ሃይማኖት በአራተኛው መቶ ዓመተ ምሕረት በቅዱስ ማርቆስ መንበር መሠረት የተቋቋመችው ጥንታዊት የኢትዮጵያ ቤተክርስ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት መሆን አለበት።

2. በማናቸውም ሃይማኖት መንፈሳዊ አገልግሎት በሚደረግበት ጊዜ ሁሉ ለ ትዮጵያና ለንጉሠ ነገሥቱ ጸሎት ይደረጋል።

ንኡስ ክፍል — 2

ስለ ዘውድ አወራረስ

አንቀጽ 10፡

በአንቀጽ 12 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የኢትዮጵያ ዘውድ ከ ዳግማዊ ምኒልክ ጀምሮ እስከ ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ተያይዞ ከመጣው ከ ሣህለ ሥላሴ ዘር ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ትውልድ ባይወጣ ይኖራል።

./.

አንቀጽ 11፡

1. የኢትዮጵያ ዘውድ ጸና ባይለይ ከወሳኙ ወይ ልጁ፡፡ በዐፄው ከፍ ፣ ሰሆ ነው ቅድሚያ እየበጠ ይተላለፋል፡፡ ንጉሠ ነገሥቱ ወይ ታች የሚጠበቀ ተወላጆች የሌሉት እንደሆነ ወይ ግን በዝምድና ወይ የረበውና በዐ ፄው ከፍተኛ ወይ ሆነው በው ይተላለፋል፡፡ ይህም በሕይወት ካልተገኘ በዐፄው ከፍተኛ ወይ ሆነው ተወላጅ ተላልፍ ከዚያም አላይ እንደተመ ለከተው ከወላጅ ወይ ልጅ፡ ልጅ በይኖርም ወይ ቅርብ ዘመድ እየተላለፈ ይቀጥላል፡፡

2. በማሕፀን ያለ ልጅ ዘውዱን ለመውረስ መብት ከተበጠቸው በዶች ተራ ገብቶ ይጠብቃል፡፡

3. የንጉሠ ነገሥቱ ቤተ ዘመድ አባሎች ኢነማ እንደሆኑ፡ የማዕርጋቸው ሁኔታ፡ ተገበራቸውና ሌላም ዝርዝር ጉዳይ በሕግ ይወሰናል፡፡

አንቀጽ 12፡

በትውልድ ኢትዮጵያውያን ከሆኑ ቤተሰብ ሕጋዊ ጋብቻ ያልተወለዱ፡ ወይም በኢትዮጵያ እርቶዶክስ ሃይማኖት የማያምኑ ዘውዱ የመውረስ መብት አይኖራቸውም፡፡ እንዲሁም ንጉሠ ነገሥቱ በራሱ ፈቃድ ወይም ለመንገሥ ከሚያበቁት ሁኔታዎች አንዱን በማጉደል ዙፋኑን የለቀቀ እንደሆነ፡ ዙፋኑ ከተለቀቀ በኋላ ተፀነሰው የተወለዱ ልጆችና ተወላጆቻቸው ዘውዱ የመውረስ መብት አይኖራቸውም፡፡.

-------3

./.

አንቀጽ 13፡
=========

ንጉሠ ነገሥቱ ዘውዱን በሚቀዳጁበት ጊዜ የሚደረገው ሥነ ሥርዓት በሕግ ይደነገጋል። ሥርዐተ ንግሡም ሲፈጸም ቀጥሎ የተመለከተውን የመሐላ ቃል ይሰጣል።

"እኛ .....ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ የንጉሠ ነገሥቱን መንግሥት ሕገ መንግሥት አክብረን እንጠብቃለን፤ ሕዝባችንን ለጥቅሙ የሚሆነውን እያበጀን በሕገ መንግሥቱና በሕጎቹ መሠረት በርኅራኄና በትዕግሥት ንጉሣዊ ተግባራችንን እንፈጽማለን የንጉሠ ነገሥት መንግሥታችንን አንድነትና ግዛቱን እንጠብቃ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ጸንተን እንኖራለን። ሕዝባችን ሥጋዊና መንፈሳዊ ደኅንነትን እንዲያገኝ በቻልነው ሁሉ እንረዳለን። ይህን የተናገርነውን ሁሉ በእውነት ለመፈጸም ሁሉን በሚችል በእግዚአብሔር ስም ምለናል። ይህንንም ለመፈጸም እግዚአብሔር ይርዳን።"

አንቀጽ 14፡
=========

ንጉሠ ነገሥቱ ቅብዐ መንግሥት ተቀብለው ዘውዱን የሚቀዳጁት የዐሥራ ስምንት ዓመት ዕድሜ ሲሞላቸው ነው። ዘውዱን በወረሱበት ጊዜ ዕድሜያቸው ከዐሥራ ስምንት ዓመት አልፎ እንደሆነ ዘውዱን ከወረሱበት ቀን ጀምሮ በአንድ ዓመት ውስጥ ቅብዐ መንግሥት ተቀብለው ዘውዱ ይቀዳጃሉ። በዓለ ንግሡ በአዲስ አበባ መናገሻ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ይፈጸ

አንቀጽ 15፡
=========

ንጉሠ ነገሥቱ በብርቱ ሕመም መታመም በብሔራዊ ሸንጎ ቢረጋገጥ ወይም በአገር ውስጥ የሌሉ እንደሆነ፣ የእንደራሴነቱ ሥራ በአልጋ ወራሹ ይካሄዳል። አልጋወራሹ በብርቱ ሕመም መታመሙ በብሔራዊ ሸንጎ ቢረጋገጥ ወይም በአገር ውስጥ የሌሉ እንደሆነ ወይም ንጉሠ ነገሥቱ ወይም አልጋወራሹ ዐሥራ ስምንት ዓመት ያልሞላቸው እንደሆነ የእንደራሴነቱ ሥራ በእንደራሴው ምክር ቤት ይካሄዳል። ንጉሠ ነገሥቱ ወይ

./.

አልጋወራሹ እንደሚያገለግሉ [illegible]
ቋሚ ነገሥታት ሥርዓትን ደንብ ይኖራል።

አንቀጽ 16፡

የእንደራሴዎች ምክር ቤት አባሎች የሚሆኑት የአልጋወራሹ ወላጆች ወይም ብፁዓን ጳጳሳት፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ሁለቱ የብሔራዊ ሸንጎ ሊቀመንበሮች፣ አፈ ንጉሡ፣ በብሔራዊ ሸንጎ የሚመረጡ [illegible] ከሠላሳ እስከ በበ የሆኑ ሁለት የንጉሠ ነገሥቱ የቅርብ ቤተ ዘመድ ናቸው።

የአልጋ ወራሹ ወላጅ ቦታ በማናቸውም ምክንያት ክፍት በሆነ ጊዜ ከንጉሠ ነገሥቱ የቅርብ ቤተ ዘመድ አንዱ ተጠሪ አባል በብሔራዊ ሸንጎ ይመረጣል። አባሎቹም ከተመረጡት ቤተ ዘመድ አንዱን በሰብሳቢነት ይመርጣሉ።

አባሎቹም ተግባራቸውን በሚገባ ለመፈጸም ቃለ መሐላ ይፈጽማሉ፡

አንቀጽ 17፡

ንጉሠ ነገሥቱ ወይም ከንጉሠ ነገሥቱ ቤተ ዘመድ መካከል አንዱ በዐረፈ ጊዜ የሚደረገው ኃዘን በሕግ ይወሰናል።

ንዑስ ክፍል — 3

ስለ ዘውዱ ንብረት

አንቀጽ 18፡

1. የንጉሠ ነገሥቱ፣ የእቴጌይቱና የአልጋወራሹ የንጉሥና የዘውድ ዕቃዎች በብሔራዊ ቅርስ ስለሆኑ፣ የማይሸጡ፣ የማይለወጡ ወይም በሌላ መንገድ የማይተላለፉ የመንግሥት ንብረቶች ናቸው።

2. ለቤተ መንግሥት አገልግሎት የሚውለው ንብረት በሕግ ተወስኖ በንጉሠ ነገሥቱ ይተዳደራል፤ ንብረቱም በሕግ ካልተፈቀደ በቀር የማይሸጥ፣

የማይለወጥና ለሌላ የማይተላለፍ ነው።

3. ንጉሠ ነገሥቱ በዚህ ሕገ መንግሥት መሠረት ሳለበት ለንጉሠ ነገሥትነት ተግባር መፈጸሚያ ከተገባር ጋራ ሙዛዛኝ የሆነ፣ አላይ ከጠቀበሌ ገቢና ጥቅም ጋራ የሚታከል በሕግ የተወሰነ ገንዘብ በየዓመቱ ከመንግሥት እየተቀበለ ያዘበታል።

4. የንጉሠ ነገሥቱና የቤተ ዘመድ የግል ንብረት የማንኛውም ኢትዮጵያዊ ንብረት በሚተዳደርበት ሕግ ይተዳደራል።

5. ንጉሠ ነገሥቱ ቤተ መንግሥቱን ይመራል። የቤተ መንግሥቱንም ሹማምንት ይሾማል፤ ይሽራል።

ክፍል — 3

ስለ ንጉሠ ነገሥቱ ሥልጣንና ተግባር

አንቀጽ ፲፩

ንጉሠ ነገሥቱ፣

1. በዚህ ሕገ መንግሥት መሠረት ተመርጠው ሊቀርቡለት ጠቅላይ ሚኒስትርን፣ ሚኒስትሮችን፣ ዳኞችንና ሌሎችንም የመንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ይሾማል።

2. በሚኒስትሮች ምክር ቤት ተወስኖ ሊቀርብለት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጉዳዮች ያከናውናል፤

   ሀ. ሕጎችን ማወጅ፣

   ለ. የኢንተርናሽናል ስምምነቶችን ማፅደቅ፣

   ሐ. የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታን፣ የጦር ጊዜ አስተዳደርን ወይም የመከላከል ጦርነትን ማወጅ፣

   መ. [illegible] መክፈቻና በመክፈቻው ሥነ ሥርዓት ላይ የዙፋን ቃል መናገር፣ ወይም እንዲነገር ማድረግ፣

./.

ሠ. ብሔራዊ ሸንጎ ከመደበኛው የስብሰባ ወራት ውጭ እንዲሰበሰብ ማድረግ ወይም የሚከፈትበትንና የሚዘጋበትን ጊዜ ማስተላለፍ፣

ረ. ለሚሾሙ አምባሳደሮች፣ ሚኒስትሮች፣ ልዩ መልእክተኞች የሹመት ደብዳቤ መስጠት፣ ከውጭ አገር መንግሥታት እየተሾሙ የሚመጡትንም የሹመት ደብዳቤ መቀበል፣

ሰ. በወንጀል ጉዳዮች ይቅርታና ምሕረት ማድረግ፣ ቅጣቶችንም ማሻሻል

ሸ. ኒሻን መሸለም፣ የመሥፍንነትንና ሌሎችንም የክብር ስሞች መስጠት

3. ሌሎችም በዚህ ሕገ መንግሥት መሠረት የተሰጠውን ተግባር ሁሉ ይፈጽማል፡

<u>አንቀጽ 20፡</u>

ንጉሠ ነገሥቱ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ ነው። የጠቅላይ አዛዥነቱንም ተግባር በሕጉ መሠረት ይፈጽማል።

ምዕራፍ ሁለት

መብት፣ ግዴታና ኃላፊነት

<u>አንቀጽ 21፡</u>

ሰዎች ሁሉ በሕግ ፊት እኩል ሆነው ይጠበቃሉ።

<u>አንቀጽ 22፡</u>

በኢትዮጵያውያን መካከል፣ በትውልድ፣ በሀብት፣ በሃይማኖት፣ በገቢ፣ በቋንቋ፣ በጾታ፣ በፖለቲካ እምነት ምክንያት በመብት ረገድ አንዳች ልዩነት አይደረግም።

./.

አንቀጽ 23፡

1. ማንኛውም ሰው ወላጆቹ ወይም ከወላጆቹ አንዳቸው ኢትዮጵያዊ ከሆኑ፣ ኢትዮጵያዊ ነው። ኢትዮጵያዊነትም ያለፈቃዱ አይወሰድበትም። ሆኖም፣ ድርብ ዜግነትን ለማስቀረት በሌላ አኳኋን በሕግ ሊወሰን ይችላል።

2. የውጭ አገር ሰዎች የኢትዮጵያ ዜግነት የሚያገኙበትና የሚያጡበት ሁኔታ በሕግ ይወሰናል።

አንቀጽ 24፡

በኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች በዚህ ሕገ መንግሥት የተጻፉትን መብቶችና ግዴታዎች እያከበሩ፣ ለፖለቲካ ዓላማ ባይውሉና የሕዝብን መልካም ጠባይ ወይም ፀጥታን ባያውኩ፣ የክርስትና፣ የእስልምና፣ ሌሎችም ሃይማኖት ከመያዝ፣ ከማክበር ሕጋዊ በውነት ያለው ማኅበር አቋቁመው ሃይማኖታቸውን ከማስፋፋት አይከለከሉም።

አንቀጽ 25፡

1. ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የሐሳብ ነፃነት አለው። ማናቸውንም ሐሳብ በንግግር፣ በጽሑፍ ወይም በሌላ ዘዴ የመግለጽና የማሰራጨት እንዲሁም ሌሎች የገለጹትን የማወቅ መብት አለው።

2. ማንኛውም ሰው በቴሌፎን፣ በቴሌግራፍ፣ በፖስታ ወይም በማንኛውም ሌላ የመገናኛ ዘዴ ሚስጢሩ እንዲጠበቅ የመነጋገርና የመላላክ መብት አለው።

3. በዚህ አንቀጽ የተመለከተው መብት የቅድሚያ ቁጥጥር ሊደረግበት የሚችለው በአንቀጽ 111፣ 112 ወይም 113 የሚጠቀሰው አዋጅ ሲያዝ ብቻ ነው። አዋጁ ቢነሳ ቁጥጥሩም አብሮ እንዲነሳ ይቆጠራል።

./.

አንቀጽ 26:

ማንኛውም ሰው ሕይወትን፣ ነፃነትን ወይም ንብረትን ያለ ሕግ አያጣም።

አንቀጽ 27:

ኢትዮጵያውያን ሁሉ በመንግሥት ፈቃድ መጠየቅ ሳያስፈልጋቸው፣ የጦር ወይም ሌላ የጠብ መሣሪያ ሳይዙ ስብሰባ ወይም በሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ መብት አላቸው። በሕዝብ አደባባይ ስብሰባ ወይም በመንገድ ላይ በሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ ገን 72 ሰዓት በቅድሚያ አግባብ ላለው ባለሥልጣን ማስታወቅ ይኖርባቸዋል። ሆኖም ስብሰባው ወይም በሰላማዊ ሰልፉ ከዚህ ባነሰ ጊዜ ውስጥ እንዲደረግ አግባብ ያለው ባለሥልጣን ሊፈቅድ ይችላል።

አንቀጽ 28:

ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በኢትዮጵያ ውስጥ ከሥፍራ ወደ ሥፍራ ለመዘዋወርና መኖሪያውንም በመረጠው የአገር ክፍል ለማድረግ መብት አለው።

አንቀጽ 29:

ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዓላማው በሃይማኖት፣ በጎሣ ወይም በሌላ ምክንያት የኢትዮጵያን አንድነት የሚነካ ካልሆነ በቀር ማናቸውንም ዓይነት ማኅበ የፖለቲካ ማኅበር ጭምር ለማቋቋምና የማኅበርም አባል ለመሆን መብት አ

አንቀጽ 30:

1. የኢትዮጵያውያን ቤተሰብ፣ ትምህርትና ማኅበራዊ ኑሮ የተመሠረተበት፣ ኅብረተሰቡም የሚጠነክርበት ስለሆነ፣ በሕግ ልዩ ጥበቃ ይደረግለታል።
2. ጋብቻ በሚጋቡት ሰዎች ስምምነት የተመሠረተ መሆን አለበት። በጋብቻ በ ኖሩበት፣ በሚፈቱበትና በሞት በሚለያዩበት ጊዜም የሁለቱ ክብር መብትና ግዴታ በእኩልነት የተጠበቀ ይሆናል።
3. ከጋብቻና ከጋብቻ ውጭ በተወለዱ ልጆች መካከል በመብትና ግዴታ ረገድ ልዩነት አይደረግም።

./.

አንቀጽ 31:

1. ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ከኢትዮጵያ ውጭ እንዲሰደድ አይገደድም:: እንዲሁም ከኢትዮጵያ ውጭ ከመሄድ ወይም ወደ ኢትዮጵያ ከመግባት አይከለከልም::

2. ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ለውጭ አገር ተላልፎ አይሰጥም::

አንቀጽ 32:

1. ማንኛውም ሰው ወንጀል ሲፈጽም እጅ ከፍንጅ ወይም እንደፈጸመ ወዲያውኑ ካልሆነ በቀር ያለፍርድ ቤት የጽሑፍ ትእዛዝ አይያዝም:: ትእዛዙም ምክንያቱን መግለጽ አለበት::

2. ማንኛውም የተያዘ ሰው እንደተያዘ ወዲያውኑ የተያዘበትን ምክንያትና ከወዳጅ ዘመዱና ከጠበቃ ጋር ለመመካከር መብት ያለው መሆኑ በሚያውቀው ቋንቋ ይነገረዋል::

3. ማንኛውም የተያዘ ሰው በተቻለ ፍጥነት ቢበዛ ከሃያ አራት ሰዓት በማይበልጥ ጊዜ·ውስጥ ቅርብ ወደ ሆነው ፍርድ ቤት መቅረብ አለበት:: ይህ የሃያ አራት ሰዓት ጊዜ የተያዘውን ሰው ከተያዘበት ቦታ በተቻለ ፍጥነት ፍርድ ቤት ለማድረስ የሚያስፈልገውን ጊዜ አይጨምርም::

4. ማንኛውም የተያዘ ሰው ተይዞ የቆየበት ጊዜ በፍርድ በሚወሰነው የእሥራት ጊዜ ውስጥ ገብቶ ይቆጠርለታል::

5. የገንዘብ መቀጮ ብቻ በሚያስቀጣ ወንጀል የተከሰሰ ማንኛውም ሰው ጉዳዩ በፍርድ እስኪወሰን ድረስ በእሥር ቤት እንዲቆይ አይደረግም::

6. ማንኛውም በወንጀል የተያዘ ወይም የተከሰሰ ሰው የተከሰሰበት ጉዳይ በሕግ መሠረት በዋስ የሚያስለቅቅ ቢሆንና የተያዘውም ሰው የዋስነትን ሥራ የማያበላሽ ከሆነ በዋስ ሆኖ የመከራከር መብት አለው:: የዋስትናው መጠን የወንጀሉን ከባድነት በማመዛዘን ተከሳሹ እንዲቀርብ የሚያስገድደውን ያህል ብቻ ሆኖ በፍርድ ቤት ይወሰናል::

./.

አንቀጽ 33፡

በወንጀል የተከሰሰ ማንኛውም ሰው፡—

1. አንቀጽ125 እንደሚፈቅደው ካልሆነ በቀር ጉዳዩ በሕግ በተገቢው ፍርድ ቤት በግልጽ ችሎት በቶሎ እንዲታይለት መብት አለው።

2. የተከሰሰበት ወንጀል በሚያስቀጣው ደንብ እንዲገለጽለት መብት አለው። እንዲሁም አማርኛ የማያውቅ ከሆነ ችሎቱ ያለው አስተርጓሚ በመንግሥት ወጪ እንዲረዳው መደረግ አለበት፡

3. መከላከያውን ለማዘጋጀት በቂ ጊዜ ለማግኘት መብት አለው።

4. ራሱ ወይም በመረጠው አማካይነት ለመከላከል መብት አለው። ሆኖም፣ ጠበቃ ለመቅጠር ያልቻለ እንደሆነ የተከሰሰበት ወንጀል ከባድ ቢሆን በመንግሥት ወጪ ፍርድ ቤት ጠበቃ ያቆምለታል።

5. የተቀጠረበት ምስክሮች ከፊቱ ቀርበው እንዲመሰክሩና ምስክሮችንም ራሱ ወይም በመረጠው አማካይነት ለመጠየቅ መብት አለው። ይመሰክሩልኛል የሚላቸውንም ምስክሮች ፍርድ ቤት ያቀርብለታል። ተከሳሹ የማቅረቢያውን ወጪ ለመክፈል ካልቻለ መንግሥት ይከፍልለታል።

አንቀጽ 34፡

ማንኛውም በወንጀል የተከሰሰ ሰው በፍርድ ቤት ካልተረጋገጠበት በቀር እንደጥፋተኛ አይቆጠርም።

አንቀጽ 35፡

ቅጣት የሚወሰነው በአጥፊው ሰው ላይ ብቻ ነው። ማንኛውም ሰው ሕግ እንደሚፈቅደውና ጥፋተኛ መሆኑን አረጋግጦ ፍርድ ቤት በሚሰጠው ውሳኔ መሠረት ካልሆነ በቀር አይቀጣም።

./.

አንቀጽ 36፡

1. ማንኛውም ሰው የተከሰሰበትን ነገር ከማድረጉ በፊት አድርጎት ወንጀል መሆኑ በሕግ ያልታወጀ ከሆነ አይከሰስበትም አይቀጣበትምም::

2. ማንኛውም ሰው ወንጀሉን በሠራበት ጊዜ ጸንቶ በነበረው ሕግ ለዚያ ወንጀል ከተወሰነው በላይ ቅጣት አይቀጣም::

አንቀጽ 37፡

ማንኛውም ሰው በአንዱ ወንጀል በፍርድ ቤት ውሳኔ ነፃ ከተለቀቀ ወይም ከተቀጣ በኋላ በዚያው ወንጀል ሁለተኛ ጊዜ አይከሰስም::

አንቀጽ 38፡

1. ማንኛውም ሰው በግርፋት ወይም በማሰቃየትና በጭካኔ በሆነ ቅጣት አይቀጣም::

2. በቅጣት መልክ የማንኛውም ኢትዮጵያዊ ንብረት አይወረስም:: ሆኖም ወንጀል የተሠራበት ወይም የወንጀል ፍሬ የሆነ ንብረት እንዲወረስ በሕግ ሊደነገግ ይችላል:: የፍትሐ ብሔርን ዕዳ ለማስከፈል ወይም በጥፋት ምክንያት ወይም ታክስና መቀጮን ለማስከፈል ከፍርድ ቤት ሥልጣን በተሰጠ ትእዛዝ መሠረት ያንዱ ሰው ንብረት ቢያዝ እንደወረሰ ሆኖ አይቆጠርም::

አንቀጽ 39፡

ማንኛውም ሰው በወንጀል በራሱ ላይ እንዲመሰክር አይገደድም::

አንቀጽ 40፡

ማንኛውም ሰው የተፈረደበትን ዕዳ ባለመክፈል የማታለል ሥራ ሠርቶ ካልተገኘ በቀር፣ ወይም ሕግን ተላልፎ የወሰደውን ገንዘብ፣ ወይም

./.

ኅብረት ወይም የተጋብነበትን መጨ አንቀጽ፣ በፍርድ ቤት ዳዘ
አምቢተኛ በሆነ በፍር፣ ወይም የሰብ የሚበላት ሕጋዊ ገቢታዎችን
ለመረከም አምቢ ከሰለ በፍር በሰዓ ጋብቻት አይጠየቅም::
ሀገሩም ዐዓ በፈቃ ገንዘብ በገኘ ጊዜ ዐዓውን በመክረል አይቻልም::

<u>አንቀጽ 41:</u>

1. በማንኛውም በው ላይ ወይም በቤቱ፣ በኅብረት ተገቢ ያልሆነ ብርበራ አይደረግበትም:: ማናቸውም ሠነድ ወይም ሌላ ዕቃ በዚህ መንገድ አይያዝበትም:: በቃለ መሐላ ወይም በማረጋገጫ የተደገፈ በቂ ምክ ንያት ከሌለ በቀር ስብርበራ ትእዛዝ ከፍርድ ቤት አይሰጥም:: ትእዛዝ ሲሰጥ የሚያዘውን ዕቃ፣ የሚበረበረውን ቦታ፣ ወይም ሰው በግልጥ ለይቶ ማመልከት አለበት::

2. በዚህ አንቀጽ መሠረት ብርበራው ህገ መንግ ገለልተኛ በሆኑ፣ ከሁለት በላይ ምስክሮች ፊት መሆን አለበት::

<u>አንቀጽ 42:</u>

በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ የሆነ ማንኛውም ሰው ጉዳዩ ለሚመለከተው የተመንግሥት መሥሪያ ቤት አቤቱታውን ለማቅረብና ለአቤቱታው የተፈጠነ ውሳኔ ለማግኘት መብት አለው::

<u>አንቀጽ 43:</u>

1. ወንጀል ሠርቷል በመባል የተያዘ ሰው፣ ዝምታ ማበል ወይም ሥቃይ አይፈጸምበትም:: የሚመረመርበት ሥርዓት በሕግ ይወሰናል:: በማ ሠቃየት፣ በዛቻ ወይም በሌላ የተገኘ ማስረጃ ሕጋዊ ውጤት የለውም:: በተያዘው ሰው ላይ ዛቻ ማበል ወይም ሥቃይ ያደረ አይፈቀድም::

. . /.

ማንኛውም ሰው ሰሊን ይችላል፡ ዝርዝሩ ርዕም ሥዩ የሚሠሩት ሰው ተገቢ ካሣውን ያገኛል፡፡

2. ማንኛውም ሰው ተይዞ ፍርድ ቤት በቀረበ ጊዜ ርዕ ፍሉ ስንም ሰሰ አይደረግም፡፡ በዋስ በሚተዳደሩ የማስረጃ መብቱ ተጠብቆ ስለ ሰው መንግሥት በሚያዝዘው ዓረፍ ቤት እንዲቀርብ ይደረጋል፡፡

ሰንቀጽ ==44፡

በማንኛውም በሥልጣን ርዕም ባለ ሰው የተፈጸመ የሚሠሩ ርዕም እን ዓይዝዋር የተከለከለ ሰው ራሱ ርዕም ባለ ሰው አማካይነት አላ ግቢ መያዣ፣ መጠሩን ርዕም ከመዝዋር መከልከሉን ለፍርድ ቤት የማመልከት መብት አለው፡፡ አፈጻጸሙን ረጅም የተገለው በሥልጣን ርዕም ሰው አመልካቹን አቅርቦ አፈጻጸሙ ሕጋዊ መሆኑን ለፍርድ ቤት ማስረዳት ካልቻለ፣ አመልካቹ ወዲያውኑ ይለቀቃል፡፡

ሰንቀጽ ==45፡

የዚህ ሕገ መንግሥት ሌሎች አንቀጾች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ኢትዮጵያውያን ነገዶችና ጎሳዎች ቋንቋቸውንና ባህላቸውን ለመጠበቅ፣ ለማዳበርና ለማበልጸግ መብት አላቸው፡፡

ሰንቀጽ ==46፡

ኢትዮጵያውያን ሁሉ በዚህ ሕገ መንግሥት መሠረት የመምረጥና የመመረጥ መብት አላቸው፡፡

ሰንቀጽ ==47፡

1. ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የሚችለውን ሥራ እየሠራ መኖር መብቱ ነው፡፡

./.

2. ማንኛውም የግል ድርጅት ሠራተኛ መብቱን፣ ጥቅሙንና ክብሩን ለሜበ ደኅና ለማስጠበቅ የሠራተኛ ማኅበር በማደራጀት ወይም በተደራጀው አባል በመሆን በኅብረት የመደራደር መብት አለው።

<u>አንቀጽ 48፡</u>

አንድ ዓይነት ሥራ ለሚሠሩ ሠራተኞች በደመወዝ ወይም በሌላ ማዕከ የሚከፈለው ዋጋ በጾታ፣ ወይም ሥራውን በቀጥታ በማይመለከት በሌላ በማናቸውም መክንያት ልዩነት አይደረግም።

<u>አንቀጽ 49፡</u>

1. ሕፃናት የኢንዱስትሪ ሥራ እንዲሠሩ አይፈቀድም።
2. አካለ መጠን ያልደረሱ ወጣቶች የሚሠሩበት ሁኔታ በሕግ ይወሰናል።

<u>አንቀጽ 50፡</u>

ማንኛውም ሰው የፍርድ ቤት ቅጣት ተወስኖበት ካልሆነ በቀር አለ ዋጋ እንዲሠራ አይገደድም።

<u>አንቀጽ 51፡</u>

1. ማንኛውም ሰው ሕገ መንግሥቱንና በሕገ መንግሥቱ መሠረት የወጡትን ሕጎች ማክበር ግዴታው ነው።
2. ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በኢትዮጵያና በኅብረተ ሰቡ ላይ የሚነሳውን ጠላት መከላከል፣ በተጠራ ጊዜ የወታደርነትና ሌላም የሕዝብ አገልግሎት መስጠት ግዴታው ነው።

<u>አንቀጽ 52፡</u>

ማንኛውም ሰው በሕግ የሚወሰነውን ግብርና ቀረጥ መክፈል ግዴታው ነ

./.

አንቀጽ 53:

1. ለጦር ኃይል አባሎች፣ በመንግሥት አገልግሎት ላይ ለሚገኙ ሌሎች ሰዎች በዚህ ምዕራፍ የተሰጡት መብትና ነፃነት የየሥራቸው ጠባይ የሚጠይቀውን ያህል ብቻ የሚቀነስበት ወይም የሚቀርበት ሁኔታ በሕግ ይወሰናል::

2. በአንቀጽ 111፣ 112 ወይም 113 የተመለከተው ሁኔታ ካልታወጀ በቀር ማንኛውም የጦር ኃይል አባል ያልሆነ ሰው በጦር ፍርድ ቤት አይከሰስም::

አንቀጽ 54:

የሌሎችን መብትና ነፃነት ለማስከበር፣ የሕዝብ ፀጥታ፣ ጤንነት፣ መልካም ጠባይ፣ ጠቅላላ ደኅንነት ወይም ጥቅም ለመጠበቅ የሚያስፈልገውን ያህል ብቻ ብሔራዊ ሸንጎ፣ ከጠቅላላ አባሎቹ ቁጥር በሁለት ሢሶ ድምፅ ብልጫ ደገፍ በሚያወጣው ሕግ ካልተወሰነ በቀር፣ ከዚህ በላይ በዚህ ምዕራፍ የተሰጡት መብቶችና ነፃነቶች በማናቸውም ሰበብ ገደብ አይቀነሱም:: ሆኖም በዚህ ሕገ መንግሥት በሌሎች አንቀጾች በሌላ አኳኋን የተወሰነው እንደተጠበቀ ይሆናል::

በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚወጡት ሕጎች የመብቶችንና የነፃነቶችን የዘወትር አሠራር የሚነካ መሆን የለባቸውም::

አንቀጽ 55:

ኢትዮጵያውያን ሁሉ ከገሩ የልማት ደረጃና ሀብት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ትምህርት፣ የጤና ጥበቃና ሥራ ማግኘት መብታቸው ስለሆነ፣ ይህንን እንዲያገኙ ማድረግና ማበረታታት፣ የመንግሥት ዓይነተኛ ዓላማና ተግባር ነው::

አንቀጽ 56:

1. መንግሥት የልማትና የትምህርት ዕድል ለኢትዮጵያውያን ሁሉ በትክክል

./.

እንዲያደርግ የሚያደርግ ኃላፊነት አለበት::

2. የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያኖች ለሥራቸውን የሚያስፈልጋቸውን ገቢዎች ቢያገኙ የአገሪቱ ደረጃ ትምህርት እንዲማሩ ማድረግ ግዴታቸው ነው::

3. በኢትዮጵያ ትምህርት ቤቶች የሚሰጠው ትምህርት በኢትዮጵያ ሥነ ሥርዓት፣ በሀል፣ ታሪክና ተፈጥሮ ላይ የተመሠረተ ይሆናል:: በመንግሥት ትም ህርት ቤቶች የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በነፃ ይሰጣል::

<u>አንቀጽ 57:</u>

1. የመንግሥትና የግል ሥራ ድርጅቶች የሥራ ሁኔታ በሠራተኞች ላይ አደ ጋን የማያስከትል ጤናቸውንና ጠቅላላ ደኅንነትን ለመጠበቅ የሚበቃ ሆኖ እንዲገኝ ሕግ ይወጣል::

2. ማንኛውም ሠራተኛ በሥራው ምክንያት በሚደርስበት አደጋ ወይም በሽታ ለሚደርስበት ጉዳት የአሠሪው ኃላፊነትና ለሠራተኛው የሚከፈለው የካሳ መጠን በሕግ ይወሰናል::

3. ከከተማ ውጭ ሠራተኞች ተቀጥረው እየሠሩ በሚኖሩበት የፋብሪካ፣ የእርሻ፣ የማዕድን ወይም ሌላ ድርጅቶች አሠሪዎች ለሠራተኞቻቸው ማኅበራዊ ስለሚገባቸው የመኖሪያ፣ የትምህርት፣ የጤና ጥበቃና ስለሌ ሎች አገልግሎቶች ሁኔታ በሕግ ይወሰናል::

<u>አንቀጽ 58:</u>

በሳይንስ፣ ሥነ ጥበብን፣ ሥነ ጽሑፍንና ኪነጥበብን ለማበልጸግና ለመደገፍ የአእምሮ ጸጋ ለተበጠው ሁሉ መንግሥት ልዩ ጥበቃና እር ዳታ ያደርግላቸዋል::

<u>አንቀጽ 59:</u>

መንግሥት የማኅበራዊ መድን ድርጅት አቋቁሞ በመንግሥትና በግል ድ

./.

ዶሩኞች እንዲሁም በግለሰቦች ተቀጥረው የሚሠሩ ድሃ ሠራተኞች ሥራ በሚፈ ሽገት ጊዜ መተዳደሪያ፣ በሚታመሙበት ጊዜ መታከሚያና በረጅም ጊዜ መጦሪያ፣ በሞታቸው ለቤተሰቦቻቸው መርጃ የሚሆን ገንዘብ ከሠራተኞችና ከአሠሪዎች የሚቆጠብበት፣ የሚተዳደርበትና የሚከፈልበት ሁኔታ በሕግ ይደነገጋል።

ምዕራፍ ሰባት

የሕግ አውጪ ዘርፍ

ክፍል — ፩

ስለ ብሔራዊ ሸንጎ

አንቀጽ 60፡

1. ብሔራዊ ሸንጎ የሕዝብ ሸንጎና የመማክርት ሸንጎን ይይዛል።
2. የኢትዮጵያን ሕዝብ ሙሉ ገዥነት የሚወክል ብሔራዊ ሸንጎ ነው። በሕግ አወጣጥም ረገድ ከፍተኛውን ሥልጣን የያዘ አካል ነው።
3. ማንኛውም ሰው በአንድ ጊዜ የሕዝብ ሸንጎና የመማክርት ሸንጎ አባል ለመሆን አይችልም።

አንቀጽ 61፡

1. ሁለቱ ሸንጎዎች የጋራ ስብሰባ የሚያደርጉት፣
   - ሀ. እያንዳንዱ የዝግጅት ወራት ሲጀመርና ሲፈጸም፣
   - ለ. በሚኒስትሮች ምክር ቤት አቅራቢነት ንጉሠ ነገሥቱ ጥሪ ሲ
   - ሐ. ከሸንጎዎቹ አንዳቸው አስፈላጊነቱን ሲወስኑ፣
   - መ. በዚህ ሕገ መንግሥት መሠረት በጋራ ስብሰባ ታይቶ የሚወ ጉዳይ ሲያጋጥም፣ ወይም
   - ሠ. ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሲጠይቅ ነው።
2. ሁለቱም ሸንጎዎች የጋራ ስብሰባ በሚያደርጉበት ጊዜ የሁለቱም ሊ መንበሮች በየዓመቱ ተራ እየገቡ በሊቀመንበርነት ስብሰባውን ይመ

./.

አንቀጽ 62፡

የብሔራዊ ሸንጎ መደበኛ የጉባኤ ጊዜ በየዓመቱ መስከረም ሀያ ሰባት ቀን ተጀምሮ እስከ ሰኔ ሠላሳ ቀን ድረስ ይቆያል። ሆኖም በምርጫ ዘመን ስለሚደረገው የጉባኤ ጊዜ በምርጫ ሕግ ይወሰናል። የስብሰባው መደበኛ ቦታ ከዐቅም በላይ የሆነ ምክንያት ካላጋጠመ አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ይሆናል።

አንቀጽ 63፡

ሸንጎዎቹ በጋራ ሆነው ጉዳይ በግል ወይም በዉል የሚያደርጉት ስብሰባ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ጥያቄ እንደ ነገሩ ሁኔታ የሕዝብ ሸንጎ፣ የመማክርት ሸንጎ፣ ወይም የጋራ ስብሰባው በድምፅ ብልጫ በሚወሰነው ውሳ ካልሆነ በቀር ለሕዝብ ዝግ አይሆንም። አንዱ ጉዳይ ምስጢር ነው ተብሎ ከተነገረ በኋላ የማናቸውም ሸንጎ አባል ወይም ማንኛውም በስብሰባው ውስጥ የነበረ ሰው ስለዚህ ነገርም ሆነ በጋዜጣ ወይም በሽሙቱ ወይም በሌላ በማናቸውም መንገድ ለሕዝብ የገለጠ እንደሆነ በሕግ መሠረት ይቀጣል።

አንቀጽ 64፡

ማንኛውም ሸንጎ ከአባሎቹ ሁለት ሢሶ ሳይገኙ በማናቸውም የመደበኛ ስብሰባ ቀን ክርክር አይጀምርም ወይም አይቀጥልም። ከአባሎቹ አብዛኞቹ ሳይኖሩ በሚቀጥለው በማናቸውም የስብሰባ ቀን ድምፅ አይሰጥ፣ ሁለቱ ሸንጎዎች የጋራ ስብሰባ በሚያደርጉበት ጊዜ ክርክር ለማድረ ድምፅ ለመስጠት ከያንዳንዱ ሸንጎ አባሎች አብዛኞቹ እንዲገኙ ያስፈልጋል።

አንቀጽ 65፡

በአንቀጽ 64 ውስጥ የተዘረዘረው የሕዝብ ሸንጎና የመማክርት ሸን

. /.

ጋሻአተ ሹሙ የብሔራዊ ሸንጎ የፌዴሬሽን ስብሰባ በተወሰነለት የ
ያልሞላ እንደሆነ ወይም ከዚያ በኋላ የናቸው ሸንጎ ወይም ሸንጎዎች
በኋላ ለሚያደርጉት ስብሰባ የሚያስፈልገው የአባሎች ቁጥር በሚገኝ
ምክንያት በርከሩን ለመጥራት ወይም ቃል ለመስጠት ያልቻሉ እንደሆነ፣
ከልተገኙት አባሎች ውስጥ የሚያስፈልገው ቁጥር እንዲገኝ ለማድረግ
በስብሰባው የተገኙት አባሎች በያንዳንዱ ሸንጎ የውስጥ ደንብ የተፈ
ቀደው ማስገደጃ ነገሮችም ለማድረግ ይችላሉ።

አንቀጽ 66፡

እያንዳንዱ ሸንጎ የየራሱን የሥራ አፈጻጸም ደንብና የውስጥ አስተ
ዳደሩን ሥነ ሥርዓት ይወስናል።

አንቀጽ 67፡

የብሔራዊ ሸንጎ አባሎች በሕግ የተወሰነውን ደመወዝ ያገኛሉ። ብሔ
ራዊ ሸንጎ የአባሎችን ደመወዝ የሚያበዛ ማናቸውንም ሕግ ያወጣ
እንደሆነ ሕጉ ለሠራበት የሚችለው ቀጥሎ የሚመረጠው የሕዝብ ሸንጎ
ከተሰበሰበ በኋላ ነው።

አንቀጽ 68፡

ማንኛውም የሸንጎ አባል ወይም ሚኒስቴር ሚኒስትርም ወይም ወኪሉ ሸን
ጎው በሚያደርገው በማናቸውም ስብሰባ ወይም ሸንጎዎች በሚያደርጉት
የወል ስብሰባ ወይም የሸንጎ ማናቸውም ኮሚቴ በሚያደርገው ስብሰባ
ላይ በቀረበው የጽሑፍ ማስረጃ ወይም በተናገረው ቃል ምክንያት አይ
ከሰስም አይወነጀልም። ሆኖም ከብሔራዊ ሸንጎ የያንዳንዱ ሸንጎ
ማንኛውም አባል ወይም ማንኛውም የስብሰባው ተከፋይ የሆነ ሰው ስለ
ሥራው አፈጻጸም በሸንጎው የተወሰኑትን የትእዛዝና የሥነ ሥርዓት ደ
ንቦች ሁሉ ማክበር አለበት። እነዚህንም ደንቦች ተላልፎ የተገኘ
ማናቸውም የሸንጎ አባል በያንዳንዱ ምክር ቤት የውስጥ ደንብ የተ
ወሰነው ይፈጸምበታል።

./.

አንቀጽ 69:

የማናቸውም ሸንጎ አባል የሆነ ማንኛውም ሰው ሸንጎው በሥራ ላይ በፍንጅ ባልተያዘ በቀር ወይም አባል የሆነበት ሸንጎ ካልፈቀደ በቀር በ[illegible] ሊያዝ ሊታሰር ወይም ለተፈረደበት የወንጀል ክስ መልስ እንዲሰጥ በፍርድ ቤት ሊጠራ አይችልም:: ሆኖም ይህ መብት በፍትሐ ብሔር ከመክሰስ አያድነውም::

አንቀጽ 70:

1. ማናቸውም የሕግ ረቂቅ፣ ከአስፈጻሚው ዘርፍ፣ ወይም በዐሥር አባሎች የተደገፈ ሲሆን ከማናቸውም ሸንጎ ይመነጫል::
2. የሕግ ረቂቅ ላንዱ ወይም ለሁለቱም ሸንጎዎች ሊቀርብ ይችላል:: ሆኖም የመንግሥትን ገቢ ገንዘብ ለማበጀት ወይም አዲስ ወይም ተጨማሪ ቀረጥ ለማስከፈል የሚቀርበው የሕግ ረቂቅ ሁሉ አስቀድሞ የሚቀርበው ለሕዝብ ሸንጎ ነው::

አንቀጽ 71:

ማናቸውም የሕግ ረቂቅ በዚህ ሕገ መንግሥት በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በቀር በስብሰባው ላይ በተገኙት አባሎች የድምፅ ብልጫ ይወሰናል:: ድምፅ እኩል ለእኩል የሆነ እንደሆነ የሊቀ መንበሩ ድምፅ ያለበት ወገን ያሸንፋል::

አንቀጽ 72:

አንደኛው ሸንጎ የተቀበለው የሕግ ረቂቅ ወዲያውኑ ለሁለተኛው ሸን ይተላለፋል:: ሁለተኛው ሸንጎ በ[illegible] ረቂቅ ከተላከበት ጊዜ ጀምሮ በሁለት ወር ውስጥ የተቀበለው እንደሆነ ለሚኒስትሮች ምክ

./.

ይተላለፋል፡፡ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የተስማማበት እንደሆነ በጠቅላይ ሚኒስትሩ አሳማኝነት በንጉሠ ነገሥቱ ስም በነጋሪት ጋዜጣ ይታወጃል፡፡

አንቀጽ 73:

አንደኛው ሸንጎ የተቀበለውን የሕግ ረቂቅ ሁለተኛው ሸንጎ በሁለት ወር ውስጥ አሻሽሎ የተቀበለው እንደሆነ፣ ረቂቁ ከነማሻሻያው ለመጀመሪያው ሸንጎ ተመልሶ ይላካል፡፡ የመጀመሪያው ሸንጎ በሠላሳ ቀን ውስጥ ረቂቁን ከነማሻሻያው የተቀበለው እንደሆነ በአንቀጽ 72 መሠረት እንዲፈጸም ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ይተላለፋል፡፡

አንቀጽ 74:

የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲአጋጥሙ የሕግ ረቂቅ በወል ጉባኤ ታይቶ ይወሰናል፡፡

1. አንደኛው ሸንጎ የተቀበለውን የሕግ ረቂቅ ሁለተኛው ሸንጎ ረቂቁ ከተላከለት ጊዜ ጀምሮ በሁለት ወር ውስጥ ያልተቀበለው እንደሆነ፣ ወይም
2. ሁለተኛው ሸንጎ አሻሽሎ የተቀበለውን የሕግ ረቂቅ የመጀመሪያው ሸንጎ በሠላሳ ቀን ውስጥ ማሻሻያውን ያልተቀበለው ወይም ምንም ውሳኔ ያላደረገበት እንደሆነ፣ ወይም
3. አንደኛው ሸንጎ በተቀበለው የሕግ ረቂቅ ላይ ሁለተኛው ሸንጎ በሁለት ወር ውስጥ ምንም ውሳኔ ያላደረገ እንደሆነ፡

የወል ጉባኤው ረቂቁን የተቀበለው እንደሆነ፣ በአንቀጽ 72 መሠረት እንዲፈጸም ረቂቁ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ይተላለፋል፡፡ ካልተቀበለው ረቂቁ ውድቅ ይሆናል፡ በዚያው የጉባኤ ወራት ለሸንጎው ዳግመኛ አይቀርብም፡፡

አንቀጽ 75:

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት የተላለፈለትን የሕግ ረቂቅ ያልተስማማበት

./.

እንደሆነ፣ አስተዳደሩን ጨምሮ ረቂቁ ከተላከለት ጊዜ ጀምሮ በአንድ ወር ውስጥ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለብሔራዊ ሸንጎ መልሶ ይልካል።

2. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ከብሔራዊ ሸንጎ በተላለፈለት የሕግ ረቂቅ ላይ በንኡስ አንቀጽ /ሀ/ መሠረት በአንድ ወር ውስጥ ያልፈጸመ እንደሆነ፣ የተላከለት የሕግ ረቂቅ ተቀባይነት እንዳገኘ ተቆጥሮ በጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካይነት በንጉሠ ነገሥቱ ስም ይታወጃል።

አንቀጽ 76፡

የሚኒስትሮች ምክር ቤት አስተዳደሩ ጨምሮበት በተመለሰው የሕግ ረቂቅ ላይ ሁለቱ ሸንጎዎች የጋራ ስብሰባ አድርገው ከተነጋገሩበት በኋላ በድምፅ ብልጫ የተቀበሉት እንደሆነ፣ ወይም ባይቀበሉት በሞ ቅረት ቀዱሞ ያደረጉትን የሕግ ረቂቅ እንዳለ ወይም አሻሽለው በሁለት ሢሶ ድምፅ ያጸኑት እንደሆነ ረቂቁ በንጉሠ ነገሥቱ ስም እንዲታወጅ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይተላለፋል። በሁለት ወር ውስጥ ይህ ካልሆነ ግን ረቂቁ ውድቅ ይሆናል። በዚያው የጉባኤ ወራት ለብሔራዊ ሸንጎ ዳግመኛ አይቀርብም።

አንቀጽ 77፡

ብሔራዊ ሸንጎ ዝግ በሆነበት ወራት አጣዳፊ ጉዳይ የተገኘ እንደሆነ የሚኒስትሮች ምክር ቤት መክሮበት ሊቀበለው ከሕገ መንግሥቱ ጋር የማይጋጩ ደንቦች በንጉሠ ነገሥቱ ሊታወጁ ይችላሉ። ብሔራዊ ሸንጎ እንደተከፈተ ደንቦቹ በአንድ ወር ውስጥ ይቀርቡለታል። ብሔራዊ ሸንጎው ደንቦቹን ያልተቀበለው እንደሆነ ባይቀበለው ከቀረበት ቀን አንስቶ የጸና መሆኑ ይቀራል። ይህም በነጋሪት ጋዜጣ ይገለጣል።

አንቀጽ 78፡

ከእያንዳንዱ ሸንጎ አባሎች መካከል በሞት በመለየት፣ በራሱ ፈቃድ ሥራ በመልቀቅ፣ ለመመረጥ የሚያበቁትን ሕጋዊ ሁኔታዎች በማጣት ወይም

./.

በሸንጎው የጸደቀ ደንብ በሚፈቅደው መሠረት በአንዱ የአባል ሀገር ገንዘብ ያለበቂ ምክንያት ከአንዱ ዐር በላይ በሥራ በተቀጠረ የአባል በታ ከፍተኛ የሆነ እንደሆነ ሲቀረው ጊዜ በምርጫ ሕግ በተወሰነው መሠረት በታች ከፍተኛ ከሆነበት ቀን እንበሶ በሁለት ዐር ወስጥ ምርጫ ተደርጎ ሌላ አባል ይተካበታል:: ሆኖም በአንቀጽ 86 እና 87 የተመለከተው ዘመን ለማለቅ የቀረው አንዱ ዓመት ብቻ ከሆነ መተካት አያስፈልግም::

<u>አንቀጽ ፸፱:</u>

እያንዳንዱ ሸንጎ አንዱ ሊቀመንበርና ሁለት ምክትል ሊቀ መንበሮች ይኖሩታል:: እነዚህም የእያንዳንዱ ሸንጎ አባሎች ከመካከላቸው በምሥጢር ድምፅ ይመርጣሉ:: የተግባራቸውና የአገልግሎታቸው ዘመን እያንዳንዱ ሸንጎ በሚያወጣው የውስጥ ደንብ ይወሰናል::

<u>አንቀጽ ፹:</u>

አባሎቹ ተገቢ መሆናቸውና አመራረጣቸው በትክክል የተፈጸመ መሆኑን ለመወሰን የሚችለው እያንዳንዱ ሸንጎ ብቻ ነው::

<u>አንቀጽ ፹፩:</u>

እያንዳንዱ ሸንጎ የራሱ ጽሕፈት ቤት ይኖረዋል:: ዋና ጸሐፊውና ሌሎቹ የጽሕፈት ቤት ሠራተኞች ተመርጠው ስለሚቀጠሩበት፣ የአገልግሎታቸውን ሁኔታና የጽሕፈት ቤቱን አሠራር እያንዳንዱ ሸንጎ ይወስናል

./.

ክፍል — 2

ስለ ሕዝብ ሸንጎ

አንቀጽ 82:

የሕዝብ ሸንጎ አባሎች የሚወከሉት በመቅላላው የኢትዮጵያን ሕዝብ አንጂ የመረጣቸውን ሕዝብና የተመረጡበትን የምርጫ አውራጃ ብቻ አይደለም::

አንቀጽ 83:

መላው ብሔረ ኢትዮጵያ በተቻለ መጠን እያንዳንዳቸው ሁለት መቶ ሺህ ነዋሪ ሕዝብ በሚገኝባቸው የምርጫ አውራጃዎች ይከፈላል:: እያንዳንዱ የምርጫ አውራጃ ሁለት የሕዝብ ሸንጎ አባሎች ይኖሩታል:: ቢሆንም ሠላሳ ሺህ ነዋሪ ሕዝብ ያለው እያንዳንዱ ከተማ አንድ የሕዝብ ሸንጎ አባል ይኖረዋል:: በተጨማሪም ከሠላሳ ሺህ በላይ ለሆነ ለእያንዳንዱ በበ ሺህ ነዋሪ ሕዝብ አንድ ተጨማሪ የሕዝብ ሸንጎ አባል ይኖረዋል:: የእያንዳንዱ የምርጫ አውራጃ አቀማመጥና ወሰን በሕግ ይወሰናል:: የምርጫ አውራጃዎች አከፋፈልና ወሰን የማናቸውንም የሕዝብ ክፍል ድምፅ አላግባብ ለመቀነስ ወይም ለመጨመር የታቀደ መሆን የለበትም::

አንቀጽ 84:

ዐሥራ ስምንት ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ዕድሜ ያላቸው፣ በማናቸውም የምርጫ አውራጃ አዘውትረው ነዋሪ የሆኑ፣ በምርጫ ሕግ መሠረት ያልተከለከሉ ኢትዮጵያውያን ሁሉ፣ በሚኖሩበት የምርጫ አውራጃ፣ የሕዝብ ሸንጎ አባሎችን ለመምረጥ መብት አላቸው:: ድምፅ አሰጣጡ በምሥጢርና በቀጥታ ሆና የሥነ ሥርዐቱ ዝርዝር በሕግ ይወሰናል::

አንቀጽ 85:

ለሕዝብ ሸንጎ አባልነት ዕጩ የሚሆን፣

./.

1. ዕድሜው ከሃያ አምስት ዓመት ያላነሰና በትምህርቱ ሊተማመኑበት የሆነ፣
2. በሰነበረት መሆን በያስፈልገው ታማኝነት በሚያሳይበት የሥራ ልም ራቸ ነፃና ሙያ ተቀጣጥ የሆነ፣
3. ፫ በምርጫ ሕግ በተሰጠው ድንጋጌ መሠረት ለተመራጭነት የሚያስችለው መብት ያልተወሰደበት

መሆን አለበት።

<u>አንቀጽ 86፡</u>

የሕዝብ ሸንጎ አባል ለአራት ዓመት ብቻ ይመረጣል። አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ይህ ጊዜ በአንቀጽ 113 መሠረት ለአንድ ዓመት ብቻ ሊራዘም ይችላል፡፡ የሕዝብ ሸንጎ አባል በአንቀጽ 65 የተዘረዘሩትን ለተመራጭነት የሚያስችሉትን ሁኔታዎች ይዞ ከተገኘ እንደገና ሊመረጥ ይችላል፡

<u>ክፍል — 3</u>

<u>ስለ መማክርት ሸንጎ</u>

<u>አንቀጽ 87፡</u>

የመማክርት ሸንጎ አባሎች የሚመረጡት በሚኒስትሮች ምክር ቤት፣ በአገር ክፍሎች አስተዳደር ምክር ቤቶችና በጠቅላይ ግዛት ዋና ከተማዎች ምክር ቤቶች ነው። በአንቀጽ 91 ንኡስ አንቀጽ 2 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የአገልግሎት ዘመናቸው ለስድስት ዓመት ይሆናል፡፡

<u>አንቀጽ 88፡</u>

የመማክርት ሸንጎ አባሎች ብዛት ዘጠና ሆኖ አመራረጣቸው እንደሚከተለ ይሆናል፡—

1. ዐሥራ አምስት አባሎች በሚኒስትሮች ምክር ቤት፣
2. ስልሳ አባሎች በዐሥራ አራቱ ጠቅላይ ግዛቶች በሚገኙ የአገር ክፍሎች አስተዳደር ምክር ቤቶችና በአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ይመረጡሉ

./..

ይህም ማለት በያንዳንዱ ጠቅላይ ግዛት የሚገኙ የአገር ክፍል አስተዳደር ምክር ቤቶች በአንድ ላይ ጠቅላይ ግዛታቸውን የሚወክሉ አራት አባሎች ቢመርጡ የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት አራት አባሎች ይመርጣሉ።

3. ዐሥራ አምስት አባሎች በጠቅላይ ግዛት ዋና ከተሞችና በአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤቶች ይመረጣሉ። ይህም ማለት የያንዳንዱ ጠቅላይ ግዛት ዋና ከተማና የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤቶች ለየራሳቸው አንድ አባል ይመርጣሉ።

4. በአገር ክፍሎች አስተዳደር ምክር ቤትና በዋና ከተሞች ምክር ቤቶች የሚመረጡ አባሎች በምርጫው ዘመን ውስጥ የሚመርጧቸው ምክር ቤቶች አባል ያልሆኑ መሆን አለባቸው።

5. የመማክርት ሸንጎ አባሎች የሚመረጡበት ዝርዝር ሁኔታ በምርጫ ሕግ ይወሰናል።

<u>አንቀጽ ፹፱፡</u>

የመማክርት ሸንጎ አባል ሆኖ የሚመረጥ ሰው በትውልድ ኢትዮጵያዊ፣ ዕድሜው ከሠላሳ አምስት ዓመት ያላነሰና በዕውቀትና በአስተያየት የበሰለ ሆኖ፣

1. በሥራው የሕዝቡን እምነትና አክብሮት ያገኘ፣
2. አገሪንና ሕዝቡን በሚያስመሰግን ሁኔታ ያገለገለ፣
3. በጠቅላላ ስለ ጠባዩና ስለሕዝባዊ አገልግሎቱ ከፍተኛ ግምት ያገኘ እና
4. በምርጫ ሕግ ውስጥ በተሰጠ በዓናቸው ውሳኔ መሠረት ለተመራጭነት የሚያስችለው መብት ያልተወሰደበት፣

መሆን አለበት።

በዚህ አንቀጽ የተነገረው እንደተጠበቀ ሆኖ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚመረጡት አባሎች ከፍተኛ ሕዝባዊ አገልግሎት ለማበርከታቸው የታወቀላቸው ወይም በልዩ ልዩ ሙያ ዕውቀታቸው ወይም በሥራ ችሎታቸው ስመ ጥር የሆኑ ሰዎች መሆን አለባቸው።

./.

አንቀጽ 90፡

በአገር ክፍል አስተዳደር ምክር ቤቶችና በዋና ከተማዎች ምክር ቤቶች የሚመረጥ የመማክርት ሸንጎ አባል በሚመረጥበት አውራጃ ዋና ከተማ ውስጥ ተቀማጭ ወይም ነዋሪ እንዲሆን አያሻም።

አንቀጽ 91፡

1. የመማክርት ሸንጎ አባሎች ሢሶ በየሁለቱ ዓመት ሥራቸውን ይለቃሉ።
2. ይህን ለማስፈጸም፣ የመማክርት ሸንጎ አባሎች፣ በሁለተኛው ስብሰባቸው፣ እኩል በሆነ በሦስት መደብ በዕጣ ይከፈላሉ። በያንዳንዱ መደብ ውስጥ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ከተመረጡት ሢሶ በአገር ክፍሎች አስተዳደር ምክር ቤት ከተመረጡት ሢሶ በዋና ከተማ ምክር ቤቶች ከተመረጡት ሢሶ ይገኝበታል። በመጀመሪያው መደብ የሚገኙ የመማክርት ሸንጎ አባሎች የሥራ ዘመን በሁለተኛው ዓመት መጨረሻ ላይ፣ በሁለተኛው መደብ የሚገኙ የመማክርት ሸንጎ አባሎች የሥራ ዘመን በአራተኛው ዓመት መጨረሻ ላይ፣ በሦስተኛው መደብ የሚገኙ የመማክርት ሸንጎ አባሎች የሥራ ዘመን በስድስተኛው ዘመን መጨረሻ ላይ ያልቃል።
3. የመማክርት ሸንጎ አባሎች በአንቀጽ 89 የተዘረዘሩትን አሟልተው ከተገኙ እንደገና ለመመረጥ ይችላሉ

ምዕራፍ አራት

ስለ አስፈጻሚው ዘርፍ

አንቀጽ 92፡

የመንግሥትን ከፍተኛ የአስፈጻሚነት ሥልጣን የያዘው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ነው።

./.

አንቀጽ 93፡

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሚኒስትሮች ሁሉ በአባልነት የሚገኙበት ነው።
ምክር ቤት በጠቅላይ ሚኒስትር ይመራል። ምክር ቤቱም የራሱን የሥራ
አፈጻጸም ደንብ ይወስናል።

አንቀጽ 94፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በብሔራዊ ሸንጎ ይመረጣል። የተመረጠውንም በው
ሸንጎው ለንጉሠ ነገሥቱ አቅርቦ የሹመቱን ሥነ ሥርዐት ያስፈጽማል።

አንቀጽ 95፡

1. የጠቅላይ ሚኒስትሩ መደበኛ የሥራ ዘመን አራት ዓመት ነው።
2. ጠቅላይ ሚኒስትሩ በተከታታይ ከተቈጠረ ለሦስት መደበኛ የሥራ ዘመን ብ
ሊያገለግል ይችላል።

አንቀጽ 96፡

1. ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሚኒስትሮችን ይመርጣል። ተመራጮቹንም ለንጉሠ ነገ
ሥቱ አቅርቦ የሹመቱን ሥነ ሥርዐት ያስፈጽማል።
2. አምባሳደሮችን፣ ሚኒስትሮችንና ልዩ መልእክተኞችን ለንጉሠ ነገሥቱ
አቅርቦ ማሾምና ከውጭ አገር እየተሾሙ የሚመጡትንም ለንጉሠ ነገሥቱ
ማቅረብ፣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ተግባር ነው።

አንቀጽ 97፡

የሚኒስትሮች ምክር ቤት፣

1. ብሔራዊ ሸንጎ ከመደበኛው የስብሰባ ወራት ውጭ እንዲሰበሰብ
ለመወሰን፣ ወይም ከ30 ቀን ሳይበልጥ ጊዜ የሚከፈትበትን (
የሚዘጋበትን ቀን እንዲተላለፍ ለመወሰን፣

./.

2. በብሔራዊ ሸንጎ ቢከፈት ስለመንግሥቱ ጉዳዮችና ኃላፊዎች ሕጎች በሎ-
ፋን ያለ የሚነገረውን ቅረብ

ይችላል::

አንቀጽ 98:

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለሚያሳልፋቸው ውሳኔዎች ሁሉ ተጠያቂነት
ለብሔራዊ ሸንጎ ነው::

አንቀጽ 99:

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በአስፈጻሚው ዘርፍ ስለሚፈጸመው የመንግሥት ሥራ
ሁሉ ተጠያቂነት፣ ለብሔራዊ ሸንጎ ነው::

አንቀጽ 100:

እያንዳንዱ ሚኒስትር በኃላፊነት ስለሚፈጸመው የመንግሥት ሥራ ሁሉ
ተጠያቂነት ለጠቅላይ ሚኒስትሩና ለብሔራዊ ሸንጎ ነው::

አንቀጽ 101:

1. የሕዝብና የመማክርት ሸንጎ በሙሉ ወይም ለብቻ ወይም በኮሚቴ በሚ-
ያደርጉት ስብሰባ፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩን ወይም ማንኛውንም ሚኒስትር
ሥራውን ስለሚመለከት ጉዳይ ለመጠየቅ ቢጠሩት፣ እንደነገሩ ሁኔታ
ራሱ ወይም ወኪሉ ተገኝቶ መልስ መስጠት አለበት::

./.

2. ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወይም ማንኛውም ሚኒስትር፣ የሕዝብና የመማክርት ሸንጎ በሙሉ ወይም ለየብቻ ወይም በኮሚቴ በሚያደርጉት ስብሰባ ላይ ተገኝቶ ሥራውን በሚመለከት ጉዳይ ለማስረዳት መብት አለው።

አንቀጽ 102:

በማናቸውም የኢትዮጵያ ክፍል፣ ከተፈጥሮም ሆነ ከሰው ኃይለት የሚነበ ከባድ አደጋ በሕዝብ ላይ ይደርባል ተብሎ ሲገመት ወይም ሲደርስ አደጋውን በአስቸኳይ ለሕዝብ በመግለጽ፣ በመንግሥት ዓቅም የሚቻለውን እርዳታ በማድረግ፣ የሕዝቡንም ገሳዊ እርዳታ በማስተባበር አደጋውን ለመከላከል አስፈጻሚው ዘርፍ ኃላፊነት አለበት።

አንቀጽ 103:

ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ሚኒስትሮችንና የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችን ለማደ ጀትና የሥራቸውን አድማሳን ለመወሰን ሥልጣን አለው። ዝርዝሩም በነጋሪት ጋዜጣ ይገለጻል።

አንቀጽ 104:

1. የፖለቲካ ባለሥልጣኖች የሆኑ፣ ከመንግሥት የሲቪል ሠራተኞች የሚለዩ በት፣ ደመወዛቸውና አበላቸው በሕግ ይወሰናል።
2. ማንኛውም የመንግሥት የሲቪል ሠራተኛ የሚቀጠርበት፣ በማዕረግ የሚያድግበት፣ ከሥራ ወደ ሥራ የሚዛወርበት፣ ከሥራ የሚታገድበት፣ ሥራ የሚለቅበትና የሚሰናበትበት፣ ጡረታ የሚያገኝበት ሁኔታ፣ እንዲሁም የአስተዳደር ሥነ ሥርዓት፣ የመንግሥት ሲቪል ሠራተኞች ማስተዳደሪያ አዶና ሠራተኞቹን የሚመለከት ማናቸውም ሌላ ጉዳይ ሁሉ በሚኒስትሮች ምክር ቤት አቅራቢነት በሕግ ይወሰናል።

አንቀጽ 105 :

ከአስፈጻሚው ዘርፍ የሚመነጨውን ማናቸውም የሕግ ረቂቅ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ከመከረበት በኋላ ለብሔራዊ ሸንጎ የሚያቀርበው በጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካይነት ነው።

አንቀጽ 106 :

ማናቸውም ሕግ በንጉሠ ነገሥቱ ስም በነጋሪት ጋዜጣ እንዲታወጅ ማድረግ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ኃላፊነት ነው።

አንቀጽ 107 :

ማናቸውም ሕግና ለሕዝብ የሚገለጥ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ በጠቅላይ ሚኒስትሩና ጉዳዩ በሚመለከተው ሚኒስትር ይፈረማል።

አንቀጽ 108 :

በወንጀል ጉዳዮች ይቅርታ ወይም ምሕረት የሚደረግላቸውን ወይም ቅጣት የሚሻሻልላቸውን በሕግ መሠረት የሚወስን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ነው።

አንቀጽ 109:

1. ማናቸውንም የኢንተርናሲዮናል ስምምነት በሚኒስትሮች ምክር ቤት አቅራቢነት ብሔራዊ ሸንጎ ከጸደቀው በኋላ የኢትዮጵያ ሕግ በመሆን በንጉሠ ነገሥቱ ስም ይታወጃል።
2. በንኡስ አንቀጽ /1/ የተመለከተውን ስምምነት ለማስፈጸም የሚደረጉ ስምምነቶች ለብሔራዊ ሸንጎ መቅረብ ባያስፈልጋቸው ጉዳዩ በሚመለከተው ባለሥልጣን በመፈረም ብቻ የጸኑ ይሆናሉ።

./.

አንቀጽ 110፡

የአገሪቱን የጦር ኃይል ብዛትና ድርጅት፣ እንዲሁም የጦር ኃይል አባ
ሎች በማዕረግ የሚያድጉበት፣ ከሥራ የሚታገዱበት፣ ሥራ የሚለቁበት፣
የሚሰናበቱበትና ጡረታ የሚያገኙበት ደንብ በሚኒስትሮች ምክር ቤት
አቅራቢነት በሕግ ይወሰናል።

አንቀጽ 111፡

በኢትዮጵያ ውስጥ በሙሉ ወይም በከፊል ከሰላማዊው የፀጥታ ጥበቃ
ቁጥጥር በላይ የሆነ ሁከት ሲፈጠር፣ ወይም ከተፈጥሮ በሚደርሱ አደ
ጋዎች የሲቪል አስተዳደር ሲናጋ፣ ወይም ከኢኮኖሚ ውድቀት የተነሳ
ከፍተኛ ችግር ሲፈጠር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ከሦስት ወር ላልበለጠ
ጊዜ የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ እንዲታወጅ ለንጉሠ ነገሥቱ ሊያቀርብ
ይችላል። ሁኔታውም ካስገደደ አዋጁ ለተወሰነ ጊዜ በብሔራዊ ሸንጎ
ሊራዘም ይችላል ።

ያስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ በሚታወጅበት ጊዜ የሚጸናው ሕግ በቅድ
ሚያ ታውጆ መገኘት አለበት።

ሆኖም በማናቸውም ጊዜ በብሔራዊ ሸንጎ ያስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ
የታወጀው አላግባብ መሆኑ ከታየው ሊያነሳው፤ ወይም ካስፈላጊው ጊዜ
በላይ የተራዘመ መሆኑ ከታየው ሊቀንሰው ይችላል።

አንቀጽ 112፡

ከውጭ በመጣ ጠላት፣ ወይም በአገር ውስጥ በሚደረግ የእርስ በርስ
ውጊያ ምክንያት በኢትዮጵያ ላይ ከባድ አደጋ ይደርሳል ተብሎ ሲገመት
ወይም ሲደርስ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ከሦስት ወር ላልበለጠ ጊዜ
የጦር ጊዜ አስተዳደር እንዲታወጅ ለንጉሠ ነገሥቱ ሊያቀርብ ይችላል፡፡
ሁኔታውም ካስገደደ አዋጁ ለተወሰነ ጊዜ በብሔራዊ ሸንጎ ሊራዘም
ይችላል ።

./.

የጦር ጊዜ አስተዳደር በሚታወጅበት ጊዜ የሚኖረው ሕግ በትፉ
ዋያ ታርም መገኘት አለበት።

ሆኖም በማናቸውም ጊዜ በፌዴራል ሸንጎ የጦር ጊዜ አስተዳደር
የታወጀው አላግባብ መስሎ ከታየው ሊስነበሩ፤ ወይም ካስፈላጊው ጊዜ
በላይ የተራዘመ መስሎ ከታየው ሊተነበሩ ይችላል።

አንቀጽ 113:

በሚኒስትሮች ምክር ቤት አቅራቢነትና በፌዴራል ሸንጎ ስምምነት ንጉሠ
ነገሥቱ የመከላከል ጦርነት ያውጃል።

ጦርነቱ በታወጀ ጊዜ ሀገር ደኅንነትና ለሕዝብ አንድነት
አስጊ የሆነውን ነገር ሁሉ ለማስወገድና መከላከያውንም አንድነቱንም ለማጠ
ለሚኒስትሮች ምክር ቤት አስፈላጊውን ነገር ሁሉ ያደርጋል።

አንቀጽ 114:

ማንኛውም ሚኒስትር ሥልጣኑን የሚለቀው፤

ሀ. ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሲያሰናብተው፤

ለ. በራሱ ፈቃድ ከሥልጣኑ ሲወርድ፤ ወይም

ሐ. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ከሥልጣን ሲወርድ ነው።

አንቀጽ 115:

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሥልጣኑን የሚለቀው፤

ሀ. መደበኛ የሥራ ጊዜው ሲፈጸም

ለ. የጠቅላይ ሚኒስትሩ ዓረቂቅ ሥራውን ሲለቅ፤

ሐ. ጠቅላይ ሚኒስትሩ የፌዴራል ሸንጎን እምነት ሲያጣ ወይም
የእምነት ድምፅ ሲነፈገው፤

መ. በጤንነት ማጣት ወይም በሞት ምክንያት የጠቅላይ ሚኒስትሩ
ቦታ ክፍት ሲሆን፤

ሠ. ጠቅላይ ሚኒስትሩ በአንቀጽ ፻፬፯ መሠረት በወንጀል እንዲከሰስ
ሲወሰን ነው።

./.

2. ከዚህ በላይ በንኡስ አንቀጽ 1 /ሀ/ ለ/ሐ/ ወይም /መ/ የተመለ
ከቱ ሁኔታ ሲያጋጥም በአርባ ቀናት ውስጥ አዲስ ጠቅላይ ሚኒስትር
ተመርጦ እስኪሾም ድረስ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በተጠባባቂነት
ሥራውን ይቀጥላል።

3. በንኡስ አንቀጽ 1 /ሠ/ የተመለከተው ሁኔታ ቢያጋጥም ግን ከአርባ
ቀን በበለጠ ጊዜ ውስጥ አዲስ ጠቅላይ ሚኒስትር ተመርጦ እስኪሾም
ድረስ የአስፈጻሚውን ዘርፍ ሥራ በተጠባባቂነት የሕዝብ ሸንጎ ፕሬ
ዚዳንት ይመራል።

4. ብሔራዊ ሸንጎ በአርባ ቀን ውስጥ አዲስ ጠቅላይ ሚኒስትር ለመምረጥ
ያልቻለ እንደሆነ ንጉሠ ነገሥቱ ብሔራዊው ሸንጎ ወዲያውኑ እንዲበተንና
ከአራት ወር በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ የአዲስ የብሔራዊ ሸንጎ አባሎች
ምርጫ እንዲደረግ ያዛል። በዚህ ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ በተጠባባቂነት
የሚያገለግል ጠቅላይ ሚኒስትር ይሾማል። ተጠባባቂ ጠቅላይ ሚኒስትሩ
ከሌሎች የመንግሥት ሹማምንት ጋር ይሠራል እንጂ የፖሊቲካ ባለሥልጣናት
አይሾምም። እንዲሁም ተጠባባቂው ጠቅላይ ሚኒስትር በዚያው በምርጫው
ዘመን ለጠቅላይ ሚኒስትርነት ወይም ለብሔራዊ ሸንጎ አባልነት እጩ ሆኖ
አይወዳደርም።

<u>አንቀጽ 116</u>፡

1. በመንግሥት ሥራ ወይም አገልግሎት ውስጥ ለመሥራት የተመረጠ፣ የተሾመ
ወይም የተቀጠረ ማንኛውም ሰው ንብረቱን በማረጋገጫ
ወይም በቃለ መሐላ ማስመዝገብ አለበት።

2. በመንግሥት ሥራ ወይም አገልግሎት ውስጥ ለመሥራት የተመረጠ፣ የተሾመ
ወይም የተቀጠረ ማንኛውም ሰው ሥልጣኑን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ
መንገድ ለግል ጥቅም ሊያውለው አይችልም። በግል ጥቅሙና ከመንግሥት
በተሰጠው ሥራ መካከል የጥቅም ግጭት ሊያስከትል የሚችል ማናቸውንም
የንግድም ሆነ ሌላ ሥራ ለመሥራት አይችልም። በተለይም የጥቅም ግጭት
የሚያስከትል ከሆነ፡—

./.

ሀ. ማናቸውንም ጥቅም ደመወዝ ወይም አበል የሚያስገኝ ሥራ ሊሠራ አይችልም።

ለ. በማናቸውም ንግድ ነክ ተግባር ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በባለአክሲዮንነት ወይም የጥቅም ተካፋይ ለመሆን አይችልም፡

ሐ. መንግሥት በሚያወጣው በማናቸውም የሽያጭ፣ የግዢ የጨረታ ውል ውስጥ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ለመግባት አይችልም።

መ. ሌላ የሆነ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለመስጠት በማሰብ በኢትዮጵያ ውስጥ ወይም ውጭ ከተደራጀው ማናቸውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ጋር የሚደረገውን ኮንሴሲዮን ወይም ሞኖፖል ለመስጠት ወይም በዚሁ በሐርድ የሚሠራ ሥራ ለመፍቀድ ወይም ለመቀበል አይችልም። እንዲሁም ከመንግሥት መሥሪያ ቤት ጋር በሚደረገው ኮንትራት ወይም ሌላ ዓይነት ስምምነት ውስጥ ሊገባ ወይም ተካፋይ ሊሆን አይችልም።

በዚህ አንቀጽ የተጠቀሰው የንብረት ማስመዝገብና የጥቅም ግጭት ጉዳይ በሕግ ይወሰናል።

<u>አንቀጽ 117</u>፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩና ሚኒስትሮች ከተሰጣቸው ሥራ ጋር በተያያዘ ጉዳይ በወንጀል የተከሰሱ እንደሆነ ነገሩ ሊታይ የሚችለው በይግባኝ ፍርድ ቤት ነው። ክሱም ሊቀርብ የሚችለው የብሔራዊ ሸንጎ የወል ጉባኤ በሚሰጠው ውሳኔ ነው። ለዚሁም አፈጻጸም በብሔራዊ ሸንጎ ልዩ ሕግ አስከባሪ ይሰየማል።

ምዕራፍ አምስት

ስለ ዳኝነት ዘርፍ

<u>አንቀጽ 118</u>፡

የዳኝነት ሥልጣን ለጠቅላይ ፍርድ ቤትና በሕግ መሠረት ለሚቋቋሙት የይግባኝና የመጀመሪያ ደረጃ የበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠ ነው። ፍርድ ቤቶችም በሕጉ መሠረት በነጻ ነጻነት ሥራ ይሠራሉ። የያንዳንዱ ፍርድ ቤት ሥልጣን በሕግ ይወሰናል።

./.

አንቀጽ 119:

ዳኞች በዳኝነት ሥራቸው ነፃ ናቸው። ከሕግ በቀር በሌላ አይመሩም።

አንቀጽ 120:

ጠቅላይ ፍርድ ቤት የአገሪቱ የመጨረሻ ፍርድ ቤት ነው። ሕገ መንግሥትን የመተርጐም የመጨረሻ ሥልጣን የጠቅላይ ፍርድ ቤት ነው። የጠቅላይ ፍርድ ቤት ሊቀመንበር አፈ ንጉሥ ይባላል።

አንቀጽ 121

1. ዳኞችን የሚመርጥና አስተዳደራቸውን የሚመራ አንድ ከፍተኛ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ይኖራል።

2. የከፍተኛ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ አባሎች
   ሀ. አፈ ንጉሥ፣ የጉባኤው ሰብሳቢ፣
   ለ. አንድ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ፣
   ሐ. የይግባኝ ፍርድ ቤት ሊቀመንበር፣
   መ. ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ፣
   ሠ. ከዚህ በላይ በተጠቀሱት አባሎች የሚመረጡ አንድ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዳኛና በመልካም ጠባያቸው የታወቁና ዳኞች ያልሆኑ ሁለት ሰዎች ይሆናሉ።

3. የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት፣ የይግባኝ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንትና ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የጉባኤው ቋሚ አባሎች ይሆናሉ። ቋሚ ያልሆኑት የጉባኤው አባሎች የአገልግሎት ዘመን፣ ጉባኤው ሥራውን የሚያከናውንበትና ንኡስ ጉባኤዎች የሚቋቋሙበት ሁኔታ በሕግ ይወሰናል።

./.

<u>አንቀጽ 122</u>:

1. ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከአፈንጉሡ ሌላ፣ ቁጥራቸው በሕግ የሚወሰን ሌሎች ዳኞች ይኖሩታል:: አፈንጉሡ በሚኒስትሮች ምክር ቤት አቅራቢነት ብሔራዊ ሸንጎ ሲቀበለው በንጉሠ ነገሥቱ ይሾማል:: አፈንጉሡ በጥፋት ምክንያት በሕዝብ ሸንጎ ክስ ቀርቦበት በመማክርት ሸንጎ አንዲሻር ካልተወሰነ ወይም በጤና ምክንያት ችሎታው የተቀነሰ መሆኑ በመማክርት ሸንጎ ካልተወሰነ በቀር ከሥራ አይወገድም፣ አንዲሁም በራሱ ፈቃድ ካልሆነ በቀር ከዳኝነት ሥራው ወደ ሌላ ሥራ አይዛወርም::

2. ስለአገር ክፍሎች የፍትሕ አስተዳደር በምዕራፍ ስምንት ያለው እንደተጠበቀ ሆኖ የጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የይግባኝ ፍርድ ቤትና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት ዳኞች በከፍተኛው የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ይመረጣሉ::

3. ዳኞች በከፍተኛ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ወይም ጉባኤው በሚወክለው ንኡስ ጉባኤ ውሳኔ ካልሆነ በቀር ከሥራ አይወገዱም፣ በዲሲፕሊን አይቀጡም፣ ከቦታ ወደ ቦታ አይዛወሩም:: በራሳቸው ፈቃድ ካልሆነ በቀር ከዳኝነት ወደ ሌላ ሥራ አይዛወሩም::

<u>አንቀጽ 123</u>:

ዳኞች በጠባያቸው መልካም አርአያነት፣ በሕግም በቂ ልምድና ችሎታ ያላቸው መሆን አለባቸው:: የዳኞች ደመወዝ፣ የሥራ ዘመን፣ የጡረታ አበልና አፈጻ ሌላም ዳኞችን የሚመለከት ጉዳይ በሕግ ይወሰናል::

<u>አንቀጽ 124</u>:

አፈንጉሡ ለዳኝነት ሥራ አመራርና ለፍርድ ቤቶች አስተዳደር አስፈላጊ የሆኑትን ሥነ ሥርዐት ነክ ደንቦችን በማውጣት ፍርድ ቤቶችን ይመራል፣ ለፍርድ ቤቶች የሚያስፈልገውን የዓመት በጀት በጊዜው አዘጋጅቶ ጠቅላላ የመንግሥት በጀት ውስጥ እንዲገባ ለአስፈጻሚው ዘርፍ ያቀርባል::

./.

በመንግሥት የሲቪል ሠራተኞች ማስተዳደሪያ ሕግ መሠረት የፍርድ ቤት ሠራተኞችን ይሾማል፣ ያዛውራል፣ በደረጃ ያሳድጋል፣ ሥነ ሥርዓትን ያስከብራል።

<u>አንቀጽ 125፡</u>

ዳኞች በግልጽ ማስቻል ስለበቸው የሕዝብ ጸጥታ የሚነካ ወይም ለሕዝቡ መልካም ጠባይ የሚያሰጋ ማስረጃ ክርክር ወይም ፍርድ ያለበት መሆኑን ዳኞች ከተስማሙ በዝግ ችሎት ሊያስችሉ ይችላሉ።

<u>አንቀጽ 126፡</u>

የጦር ፍርድ ቤት የሚደራጅበት ሁኔታ፣ ሥልጣኑና ተግባሩ በሕግ ይወሰናል።

ምዕራፍ ስድስት

ስለ ኢኮኖሚና ፋይናንስ

<u>አንቀጽ 127፡</u>

የኢትዮጵያ ገንዘብ በኢትዮጵያ ብር የተመነ ይሆናል። ሕግ በሚወስነው መሠረት ገንዘብ እንዲቀረጽ፣ እንዲታተምና እንዲወጣ ማድረግ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ሥልጣን ነው። የውጭ አገር መንዛሪ ተቀማጭ ገንዘብ አጠቃቀም የንግድ ባንኮችና የገንዘብ ድርጅቶች ቁጥጥር በሕግ በተወሰነው መሠረት ይሆናል። የብሔራዊ ባንክ አዛዥ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ተመርጦ ይሾማል።

<u>አንቀጽ 128፡</u>

1. ማናቸውም የመንግሥት ገቢና ቀረጥ በሕግ መሠረት ካልሆነ በቀር

./.

ሊሰበሰብ፣ ሊቀረጥ፣ የግብሩም ሆነ የቀረጡ መጠን ሊጨመር፣ ሊቀነስ፣ ሊሠረዝ ወይም በይበረል እንዲቀር ለመፍቀድ አይቻልም። የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ልዩ ልዩ ድርጅቶች ለሚሰጡት አገልግሎት በሕግ መሠረት ተመጣጣኝ ዋጋ ለማስከፈል ይቻላል።

2. የግብርና የቀረጥ አመዳደብ በገቢና በሀብት ረገድ ያለውን ከፍተኛ አለመመጣጠን የሚገታ መሆን አለበት።

አንቀጽ 129፡

ማናቸውም የመንግሥት ገቢ በበጀት ሕግ እንደተወሰነው ካልሆነ በቀር ወጪ ሊሆን አይችልም። የበጀት ዓመት በሕግ ይወሰናል። የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለሚቀጥለው የበጀት ዓመት በሥራ ላይ እንዲውል የሚያስፈልገውን የሥራ ፕሮግራም፣ እንዲሁም ወጪና ገቢ ዋና የበጀት ሕግ ረቂቅ በጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካይነት ለሕዝብ ሸንጎ ያቀርባል።

አንቀጽ 130፡

እያንዳንዱ ሸንጎ የቀረበለትን የሥራ ፕሮግራምና የበጀት ሕግ ረቂቅ መርምሮ ስለወጪው በጀት በየአርእስቱ ድምፅ ይሰጥበታል። ብሔራዊ ሸንጎ በበጀት ረቂቅ ከቀረበለት ጠቅላላ የመንግሥት ወጪ በማናቸውም አኳኋን ጭማሪ ወጪ መፍቀድ አይችልም። ለድንገተኛ ወጪ በበጀት የሚያዘው በምንም አኳኋን ከጠቅላላው የመደበኛና የካፒታል ወጪ በጀት በመቶ ፲ ሊበልጥ አይችልም። ብሔራዊ ሸንጎ ያጸደቀውን የበጀት ረቂቅ አጼ ቢያነሱ በጀቱ ሥራ ላይ ከሚውልበት የበጀት ዓመት አንድ ወር አስቀድሞ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ይልካል። ከመደበኛ ወይ ከካፒታል፣ ከአርእስት ወይም ንኡስ አርእስት ወደ ሌላ አርእስት ወይም ንኡስ አርእስት ወጪ ማዛወር የሚቻልበት ሁኔታ በበጀት ሕግ ይወሰናል።

የተወሰነ የካፒታል ወጪ በተለይም ፊዳትን በሚመለከት ጉዳይ ከሦስት የበጀት ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ወጪ እንዲሆን በበጀት ሕግ ሊፈቀድ ይችላል።

./.

አንቀጽ 131:

በአንቀጽ 130 በተመለከተው መሠረት የቀረበው የበጀት ሕግ ረቂቅ አዲሱ የበጀት ዓመት ከመጀመሩ በፊት ያልፀደቀ እንደሆነ እስኪፀድቅ ድረስ የቀደመው ዓመት በጀት በሥራበት ይቆያል::

አንቀጽ 132.

ለማናቸውም የበጀት ዓመት ወጪ በበጀት አዋጅ ከተፈቀደው በላይ ወጪ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ተጨማሪ የበጀት ረቂቅ አዘጋጅቶ በጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካይነት ለብሔራዊ ሸንጎ ያቀርባል:: ብሔራዊ ሸንጎ ተጨማሪው በጀት በቀረበለት በአንዱ ወር ውስጥ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል::

አንቀጽ 133:

1. በሕግ ካልተፈቀደ በቀር ማናቸውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ራሱን ችሎ የሚተዳደር መንግሥታዊ ድርጅትና በርዱ እንዲሁም የአገር ክፍሎችና የከተሞች አስተዳደር፣ በንግድ ማኅበር መልክ የተዋጣ ሒሳብ አንድ ከመቶ ወይም ከዚያ በላይ የመንግሥት ንብረት የሆነ የንግድ ድርጅት ማናቸውም ዓይነት የብድር ውል መዋዋል ወይም ዋስትና ሆነ ማረጋገጫ መስጠት አይችሉም:: ሆኖም ይህ አንቀጽ ባንኮች የንግዱን ሥራ ለማካሄድ የሚያደርጉትን የብድርና የገንዘብ ክፍያ ሠነድ አይመለከትም::
2. ሕግ በሚፈቅደው መሠረት መንግሥት የአጭር ጊዜ የግምጃ ቤት ሠነድና የረጅም ጊዜ ሠነድ ለማውጣት ይችላል::

አንቀጽ 134:

እያንዳንዱ የበጀት ዓመት በተፈጸመ በአራት ወር ውስጥ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለዚያው ለተፈጸመው ዓመት እስከመጨረሻው ቀን ድረስ

./.

ያለውን የመንግሥትን የገንዘብ አቋም በበጀት ያስያዘውን የሥራ ውጤት ገቢና ወጪ ቁጥር የሚያመለክት መግለጫ በዝርዝር ለብሔራዊ ሸንጎ ያቀርባል:: መግለጫው ወዲያውኑ ለዋናው ኦዲተር ይተላለፋል:: ዋናው ኦዲተርም ስለ መግለጫው ያለውን አስተያየት በአራት ወር ውስጥ ለብሔራዊ ሸንጎ ያቀርባል:: ብሔራዊ ሸንጎው ዋናው ኦዲተር በቀረበለት ሪፖርት ላይ መክር ውሳኔ ይሰጥበታል::

አንቀጽ 135:

በሚኒስትሮች ምክር ቤት አቅራቢነት ብሔራዊ ሸንጎ በድምፅ ብልጫ መርጦ የሚሾመው አንድ ዋና ኦዲተር ይኖራል:: ኦዲተሩም በከፍተኛ ጠባዩ የታወቀና ለሙያው ተፈላጊው ዕውቀትና ችሎታ ያለው ሰው መሆን አለበት:: ኃላፊነቱ ለብሔራዊ ሸንጎ ብቻ ነው:: የሥራው ዘመን፣ የሥራው ሁኔታና ተግባሩ በሕግ ይወሰናል::

ምዕራፍ ሰባት

ስለ ንብረት

አንቀጽ 136:

1. መንግሥት እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በአካባቢው አቅም ራሱን ችሎ እንዲኖር መንገድ መፈለግ ተግባሩ ነው::
2. ኑሮውን በግብርና ያደረገ ኢትዮጵያዊ በግልም ሆነ በኅብረት የመንግሥት መሬት በባለይዞታ የመሆንና ሕግ በሚፈቅደው መሠረት ራሱ በመረቱ የመጠቀም መብት አለው::
3. መሬት ለኢትዮጵያውያን ሁሉ የተሰጠ የተፈጥሮ ሀብት በመሆኑ መንግሥት እንደየአካባቢው ሁኔታ የመሬትን አጠቃቀም በግልም ሆነ በሕብረትበባለቤትነት ሊያዝ የሚችለውን መሬት ጣራና ወሰን በሕግ ያስወስናል::

./.

4. ማንኛውም ሰው ሕግን በይተላለፍ የንብረት ባለቤት ለመሆን መብት አለው። እንዲሁ ያለው ንብረት ለሕዝብ ጠቅላላ ጥቅም ሲውል አገልግሎት ክፍሉ ስለሚወሰንበት ሁኔታ በሕግ ይወሰናል። ሆኖም ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት ተገቢ ካሳ ሳይከፈልበት ንብረቱ አይወሰድም።

አንቀጽ 137:

1. ማናቸውም የብሔረ ኢትዮጵያ ባሕር፣ ጠረፍ፣ ሐይቅ፣ ወንዝ፣ ጅረት፣ ጠረፍ፣ ወደብ፣ ደን፣ ከመሬት ውስጥና ከዚሁ በታች የሚገኝ የተፈጥሮ ሀብትና የማዕድን ክምችት ሁሉ፣ የአየር ክልሎችና አነበበት አዕዋፍና ናሠሠ ውስጥ ፍጥረቶች ጭምር ባለቤትነታቸው ለሌላ ሰው ወይም ድርጅት የ ይተላለፍ፣ ለጠቅላላው ሕዝብ ጥቅም የሚውሉ የመንግሥት ንብረቶች ናቸው።

2. በመንግሥት ስም የተያዘ፣ በሌላ ባለንብረት በግል፣ በጋራ ወይም በንብረት ያልተያዘ፣ የተለቀቀና በገበሬ ጠፍነት በመንግሥት እጅ የተያዘ መሬት ሁሉ እንዲሁም ይዞታው ለሌላ ሰው ወይም ድርጅት ሊተላለፍ የሚችል ቢሆን፣ ባለቤትነቱ ግን በማናቸውም አኳኋን ለሌላ የማይተላለፍ የመንግሥት ንብረት ነው።

3. በአንቀጽ 136 እና በዚህ አንቀጽ የተጠቀሱት የተፈጥሮ ሀብቶች ለአሁንና ለሚከተለው የኢትዮጵያ ትውልድ የተከበረ ቅርስ ስለሆኑ በሰመልኪዎ ጥበቃቸውና አስተዳደራቸው፣ ለጠቅላላው ሕዝብ ጥቅም ስለ ሚውልበት ዘዴ በሕግ መሠረት የሚያስፈልገውን ሁሉ መፈጸም የመንግሥት ተግባር ነው።

አንቀጽ 138:

1. መንግሥት ለሕብረተ ሰቡ መሠረታዊ አገልግሎት የሚሰጠውን ድርጅት ሁሉ የመቆጣጠርና አገልግሎት እንዲስፋፋ የማድረግ ኃላፊነት ስላለበት እንደ ኤሌክትሪክ መብራት ኃይል፣ መገናኛ፣ ማመላለሻ፣ ውሃና የ[illegible] የመሳሰሉትና የእነዚህም ጠባይ ያላቸው የኢንዱስትሪ እንቅስቃሴ ማለት ዋና ተግባሮች ሁሉ አገልግሎታቸው ለሕዝብ የሚዳረስበትና የሚስፋፋበት

./.

አስፈላጊው ሆኖ ሲገኝ በመንግሥት ባለቤትነት የሚተዳደሩበት ሁኔታ በሕግ ይወሰናል።

2. የግል ባለንብረቶች የኢንዱስትሪ፣ የእርሻ፣ የንግድና የሌላም ሥራ ውጤት በማበርከት ያላቸውን ጠቃሚ የሆነ ማኅበራዊ ድርሻ መንግሥት በመገንዘብ አስፈላጊውን ጥበቃና ድጋፍ ያደርግላቸዋል።

<u>አንቀጽ 139</u>:

በመንግሥት፣ በግል ሰዎች፣ በሃይማኖትና በሌሎች ድርጅቶች ይዞታ ሥር የሚገኙት ባህላዊና ታሪካዊ ቅርሶችና ሥፍራዎች የኢትዮጵያ ሕዝብ የተከበሩ ቅርሶች ስለሆኑ፣ ሕግ በሚወስነው መሠረት መንግሥት መዝገብ አስፈላጊውን ቁጥጥርና ጥበቃ ያደርጋል።

ምዕራፍ ስምንት

ስለ አገር ክፍሎችና ከተማዎች

<u>አንቀጽ 140</u>:

የአገር ክፍሎችና ከተማዎች ራሳቸውን የሚያስተዳድሩበት ሥልጣን ይኖራቸዋል። የአገር ክፍሎች ከተማዎች የውስጥ አስተዳደር ሕግ በሚወስነው መሠረት በክልላቸው ውስጥ የአስተዳደር፣ የዳኝነትና የሕግ ማውጣት ሥልጣን ይኖራቸዋል።

<u>አንቀጽ 141</u>:

የውስጥ አስተዳደር ሕግ ለአገር ክፍሎችና ለከተማዎች ከሚመደብላቸው ሥራዎች መካከል የሚከተሉት ይገኛሉ:—

1. መማክርትና የአስተዳደር ሹሞችን መምረጥ፣ የበታች ፍርድ ቤት ዳኞችን መሾም፣

./.

2. የእርሻዎችን የገጠሬዊ ኑሮ የሚያሻሽሉ ዕቅዶችን ማስፈጸም፤

3. የኅብረቱ ወገኖችን ማመሳሰያ ዘዴዎችን ማስረፈት፤

4. የጤና ጥበቃ፣ የትምህርትና ሌሎችንም ሰዋዊ አገልግሎቶችን መፈጸም፤

5. ሕዝባዊ ፀጥታን ማስጠበቅ፤

6. በቀበሌ በተቋቋሙ አማካይነት የሚተዳደሩበትን የገበያ ሥርዐት ማውጣት፤

7. ግብርንና ለልዩ ልዩ አገልግሎቶች የሚወሰነውን ዋጋ መሰብሰብ፤

አንቀጽ 142፤

የአገር ክፍሎችና ከተማዎች በሕግ ለተመደበላቸው ሥራ አፈጻጸም እንደ አስፈላጊነቱ ተገቢ ማገዣ ገንዘብ ከመንግሥት ያገኛሉ።

ምዕራፍ ዘጠኝ

የሕዝብ እንባ ጠባቂ

አንቀጽ 143፤

በአስተዳደር ረገድ የሚደርሱትን የሥራ አፈጻጸም ጉድለቶች በራሱ ተነሳሽነት ወይም የግል አቤቱታ ሲቀርብለት መርምሮ እንዳስፈላጊነቱ አገባብ ላላቸው ባለሥልጣን ማሳሰቢያ የሚያቀርብና ኃላፊነቱም ለብሔራዊ ሸንጎ ብቻ የሆነ ከፍተኛ ጠባይና በቂ ችሎታ ያለው እንባ ጠባቂ በብሔራዊ ሸንጎ ይሾማል።

./.

አንቀጽ 144 :

አንበ ጠባቂው የራሱን ጽሕፈት ቤት ለማደራጀት በመንግሥት የሲቪል ሠራተኞች ማስተዳደሪያ ሕግ መሠረት ሠራተኞችን ለማስተዳደር ለሥራው አስፈላጊ የሚሆኑትን ወረቀቶች ከማናቸውም ቦታ ፋይሎችን ለመሰብሰብ ሥልጣን ይኖረዋል:: ስለአንዳንድ አስፈላጊ ጉዳዮች በማናቸውም ጊዜ ልዩ መግለጫ፣ ስለጠቅላላ ሥራው ዓመታዊ መግለጫ ለጠቅላይ ሚኒስትሩና ለብሔራዊ ሸንጎ ያቀርባል::

አንቀጽ 145 :

አንበ ጠባቂው በሥራው ረገድ ከማናቸውም ተጽዕኖ ነፃ ነው:: አንበ ጠባቂው በጥፋት ምክንያት በሕዝብ ሸንጎ ክስ ቀርቦበት የመማክርት ሸንጎ እንዲሻር ካልወሰነ ወይም በጤና ምክንያት ችሎታው የተቀነሰ መሆኑ በመማክርት ሸንጎ ካልተወሰነ በቀር ከሥራ አይወገድም፣ እንዲሁም በራሱ ፈቃድ ካልሆነ በቀር ወደሌላ ሥራ አይዛወርም::

አንቀጽ 146 :

የአንበ ጠባቂው ደመወዝ፣ የሥራ ዘመን፣ የጡረታ አበልና የጡረታ ዕድሜ፣ የጽሕፈት ቤቱ አቋም፣ ሥልጣኑና ተግባሩ በሕግ ይወሰናል::

ምዕራፍ ሃያ

ልዩ ልዩ ውሳኔዎች

አንቀጽ 147 :

የብሔራዊ ሸንጎና የሚኒስትሮች ምክር ቤት አባሎች፣ ዳኞች፣ የአገር ክፍሎችና የከተማዎች ባለሥልጣኖች፣ ዋናው ኦዲተርና አንበ ጠባቂው እንዲሁም ሌሎች ባለሥልጣኖች በዚህ ሕገ መንግሥት መሠረት የተመደቡበትን ሥራ በሚገባ ለማከናወን ./.

ሥራቸውን ከመጀመራቸው በፊት ቃለ መሐላ ይፈጽማሉ።

አንቀጽ 148:

ይህ ሕገ መንግሥት የአገሪቱ የበላይ ሕግ ነው። ማናቸውም ሕግ ወይም ውሳኔ ከዚህ ሕገ መንግሥት ጋር የማይስማማ ሲሆን ውድቅ ይሆናል። .

አንቀጽ 149:

የዚህ ሕገ መንግሥት ማሻሻያ ሐሳብ በሕዝብ ምክር ቤት በአምሳ አባሎች፤ ወይም በመማክርት ሸንጎ ሀያ አባሎች ድጋፍ ወይም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ሊቀርብ ይችላል። ሕገ መንግሥቱ የሚሻሻለው የሕዝብና የመማክርት ሸንጎ አባሎች ለየብቻቸው በተሰበሰቡበት የማሻሻያውን ሐሳብ ከጠቅላላ የአባሎች ቁጥር ሁለት እጅ ቢደግፉት ነው። እንዲሁም የማሻሻያውን ሐሳብ ከሁለቱ ሸንጎዎች አንደኛው ተፈላጊውን የድምፅ ድጋፍ ያላገኘው እንደሆነ ወይም በአንደኛው ሸንጎ ያለፈ የሕግ ረቂቅ በሌላው ሸንጎ የተሻሻለ እንደሆነ ሁለቱም ሸንጎዎች የጋራ ስብሰባ አድርገው ከብሔራዊ ሸንጎ አባሎች ጠቅላላ ቁጥር ሁለት እጅ ቢደግፉት ሊሻሻል ይችላል። ሆኖም እያንዳንዱ ሸንጎ ወይም የጋራ ስብሰባው በማሻሻያው ረቂቅ ላይ ከተነጋገረና ከተቀበለው በኋላ ቢያንስ የሦስት ወር ጊዜ ካላለፈ በቀር የመጨረሻ ድምፅ አይሰጥበትም።

ምዕራፍ ዐሥራ አንድ

የመሸጋገሪያ ውሳኔዎች

አንቀጽ 150:

የዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 11 ስለ ዙፋንና ዘውድ አወራረስ የወጣውን ትዕዛዝ ቁጥር 91/1966 አይሽረውም።

./.

አንቀጽ 151:

ይህ ሕገ መንግሥት ሲታወጅ:—

1. የብሔራዊ ሸንጎ የምርጫ ሕግ አብሮ ይታወጃል፤
2. በሥራ ላይ የሚገኘው ምክር ቤት የስብሰባ ሥራት ፍጻሜ ይሆናል፤
3. ከአራት ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የሕዝብ ሸንጎ አባሎች ምርጫ ይደረጋል::

አንቀጽ 152:

የአገር ክፍሎችና የከተማዎች የውስጥ አስተዳደር ተደራጅቶ የመማክርት ሸንጎ አባሎች እስኪመረጡ ድረስ የሕዝብ ሸንጎ እንደ ብሔራዊ ሸንጎ ሆኖ ይሠራል:: ሆኖም የመማክርት ሸንጎ አባሎች ከሁለት ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ መመረጥ አለባቸው::

አንቀጽ 153:

ይህ ሕገ መንግሥት የሚመለከታቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፣ ፍርድ ቤቶች፣ ድርጅቶችና ባለሥልጣኖች በዚህ ሕገ መንግሥት መሠረት እስኪተኩ ድረስ ሕገ መንግሥቱ መጽናቱ ብቻ በሥራቸው ላይ ከመቆየት አያግዳቸውም:: ሕገ መንግሥቱ የማያውቃቸው ግን ሕገ መንግሥቱ ሲጸና ሥራቸውን ያቆማሉ:: ውዝፍ ሥራም የሚያስረክቡበትን መንገድ አግባብ ያለው ባለሥልጣን ይወስናል::

አንቀጽ 154:

ከዚህ ሕገ መንግሥት ጋር ተቃራኒ ያልሆነ አስቀድሞ የጸና ሕግ በአንቀጽ 5፱ በተመለከተው ሁኔታ ሡብ ፉምጽ አሳሰረው በማለት ብቻ ውድቅ አይሆንም::

=/=//=

የጉባኤው ተካፋዮች

1. አቶ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ .... ሊቀ መንበር ________
2. " አማኑኤል አብደሚካኤል .... ም/ሊቀ መንበር ________
3. ዶክተር አብርሃም ደምወዝ .... አባልና ሪፖርተር ________
4. አቶ ወርቁ ተፈራ .... " " ________
5. " ነጋሽ ገብረ ማርያም .... " ቃለ አቀባይ ________
6. ቢትወደድ አስፍሐ ወልደ ሚካኤል .... " ________
7. አቶ ይልማ ዴሬሳ .... " ________
8. " አበበ ረታ .... " ________
9. " ሐዲስ ዓለማየሁ .... " ________
10. ደጃ. ግርማቸው ተክለ ሐዋርያት .... " ________
11. ብላታ ተርፌ ሸዋዬ .... " ________
12. አፈንጉሥ ቀጣው ይታጠቁ .... " ________
13. ብላታ ማትያስ ኀለ ተጋርቁ .... " ________
14. አፈንጉሥ ታደሰ መንገሻ .... " ________
15. አቶ ጉይ ቶም. ጳግርስ .... " ________
16. ወይዘሪት ዶኒት አምሩ .... " ________
17. አቶ አሰፋ ሊበን .... " ________
18. ዶክተር አክሊሉ ሀብቴ .... " ________
19. ቀኛ. አበጉሳ አዘዘ ቢክ መጠዶ .... " ________
20. አቶ ተፈራ ደገፌ .... " ________
21. መላከ ሰላም ተክለ ተብርሃን ወ/አ የሱስ .... " ________
22. ሐጂ መሐመድ ሳኒ .... " ________
23. ሐጂ ዩሱፍ አብዱራህማን .... " ________
24. ፊታ. ሐንዶ ከራር .... " ________
25. " ገብረ ሕይወት ወልደ ሐዋርያት .... " ________
26. አቶ ብርሃኑ ዋቅያ .... " ________
27. አቶ ፍሥሐ ባይሁ .... " ________
28. " ፍሥሐ ጸዮን ተክሉ .... " ________
29. ዶክተር ኃይሌ ወልደ ሚካኤል .... " ________
30. [illegible] ወንዳየን ዎሐረቱ .... " ________